# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 331 ነሐሴ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# አዲሱ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት ይዟቸው የሚመጣቸው በረከቶች

**መስከረም ሰይፉ**

**ዜና ትንታኔ**

በዓለም ላይ የተለያዩ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓቶች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ የገንዘብ ዋጋ መጠን በማእከላዊ ባንክ የሚወሰንበት፣ የገንዘብ ዋጋ በገበያ ሥርዓቱ የሚወሰንበት እንዲሁም ማእከላዊ ባንክ እንደ አስፈላጊነቱ ጣልቃ የሚገባበት ሥርዓቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ኢትዮጵያም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የውጭ ምንዛሪ ተመን በብሔራዊ ባንክ የሚወሰንበት ሥርዓት ትከተል የነበረ ሲሆን፤ ከሰሞኑ መንግሥት ይፋ ባደረገው በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት "የውጭ ምንዛሪ ግብይት በገበያው አማካኝነት እንዲበየን" ማድረጉ ተገልጿል።

በዚህም የውጭ ምንዛሪ ተመን በገበያ የሚወሰንበት (ፍሎቲንግ ኤክስቼንጅ ሬት) ሥርዓት ፈቷን ካዞረች አንድ ሳምንትን ተሻግራለች፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም የውጭ ምንዛሪ ተመን በገበያ መወሰን (ፍሎቲንግ ኤክስቼንጅ ሬት) ማለት ምን ማለት ነው? የገንዘብ አቅም ማዳከም (ፍሎቲንግ ከዲቫሉዌት) ጋር በምን ይለያል? የውጭ ምንዛሪ ሥርዓቱ መቀየሩ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ምን አይነት አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች ይኖሩታል? እና ለሥርዓቱ ውጤታማነትስ ምን መደረግ ይኖርበታል? በሚሉ ሃሳቦች የዘርፉ ምሁራንን አነጋግሯል፡፡

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የልማት እቅድና የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ

አዲሱ የውጭ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢንሹራንስ ዘርፉ ዕድል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

**ዜና ትንታኔ**

በኢትዮጵያ 18 የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይገኛሉ። ከቴክኖሎጂና ከአዲስ ግኝት ጋር አብሮ ማደግ የሚጠበቅበት ይህ ዘርፍ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት (ጂዲፒ) ያለው አስተዋጽኦ አንድ በመቶ ብቻ እንደሆነ ይነገራል። የኢንሹራንስ ዘርፉ ስለምን አላደገም? ዘርፉን ለማሳደግ ምን እየተሠራ ነው? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ የዘርፉ ባለሙያዎች ሃሳባቸውን አካፍለውናል፡፡

በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ከ20 ዓመታት በላይ ያገለገሉት የናይል ኢንሹራንስ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ በለጠ ተፈራ እንደሚገልጹት፤ ኢንሹራንስ የመክፈል አቅም እስካለው ድረስ፣ ልክ እንደ ቤት ኪራይና ትምህርት ቤት ክፍያ ወይም አንዳንድ ወጪዎችን መሸፈን የሚችል ሰው ከትንሽ እስከ ትልቅ መግዛት የሚችለው ነገር ነው።

በነበራቸው የሥራ ቆይታ በተለይም የእውቀት ዘርፉን ከመምራት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ክፍተት እንደሚታይ መመልከታቸውን የሚያነሱት አቶ በለጠ፤ ከ1983 ዓ.ም በኋላ አብዛኞቹ የግል ኢንሹራንስ ድርጅቶች የተመሰረቱት



አቶ በለጠ ተፈራ



አቶ ያሬድ ሞላ



አቶ ጌታቸው በሻወረድ

ከመድን ድርጅት በወጡ ግለሰቦች መሆኑን ይናገራሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ከሚያስገኘው ትርፍ፣ የሰው ኃይልና ከሌሎች መመዘኛዎች አንጻር እጅጉን ዝቅተኛ አፈጻጸም በማስመዝገብ ላይ መሆኑን የሚናገሩት አቶ በለጠ፤ የኢንሹራንስ ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ አንድ በመቶ ብቻ እንደሆነ በመጥቀስ ዘርፉ በአግባቡ ባለ መመራቱ በሚፈለገው ልክ ማደግ እንዳልቻለ ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ በለጠ ገለጻ፤ በተለይም በሀገር ደረጃ የኢንሹራንስ ተቋማትን መምራት የሚችሉ ብቁ ሙያተኞች ጥቂት ናቸው፡፡ በዋናነትም የህይወት መድን (አክቿሪ) ሊሠራ የሚችል አንድም ሙያተኛ በሀገር ውስጥ ባለመኖሩ ከኬኒያ በሚመጡ ሙያተኞች ነው የሚሠራው፡፡

በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በብሄራዊ ባንክ የሚመራ የኢንሹራንስ ስልጠና የሚሰጥ ተቋም የነበረ ቢሆንም ማደግና መስፋፋት ሲገባው በማይታወቅ ምክንያት ተቋርጧል። ኢንሹራንስ እራሱን የቻለ የሙያ ዘርፍ በመሆኑ በዘርፉ የሰለጠኑ ሙያተኞችን ለማፍራት የሚያስችል ኢንስቲትዩት

የኢንሹራንስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia







# ለችግር ለተጋለጡ ወገኖች ፈጥኖ ደራሽ

**አማን ረሺድ**

**ዜና ትንታኔ**

የተለያየ ገጽታን የተላበሰችው አዲስ አበባ እንዳንዶች ኑሮ ሞልቶላቸው በተድላ ሲኖሩ በርካቶች ደግሞ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን ለመምራት የሚቸገሩባት ከተማ መሆኗ ገሃድ የወጣ ሃቅ ነው፡፡

ነዋሪዎቿ የተሻለ ኑሮ ለመምራት ቢፈልጉም ከአቅም ማነስ የተነሳ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተዳረጉ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። እነዚህን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ ወገኖችን በዘላቂነት ማቋቋምና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ምን ሚና ይኖረዋል? ተግዳሮቶችስ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህበራዊ ትረስት ፈንድ ጽህፈት ቤት ኃላፊና የዘርፉን ባለሙያዎች ጠይቀን ሃሳባቸውን ሰጥተውናል።

አቶ ኤፍሬም አሰፋ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህበራዊ ትረስት ፈንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ፤ በመዲናዋ የሚኖሩ በርካታ ዜጎች በተለያዩ ምክንያቶች ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በዘላቂነት ማቋቋም፣ የማህበራዊ ችግር ተጋላጭነትን መከላከል፣ የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ሴቶችና ወጣቶችን መደገፍ መቻል ለዜጎች ደስታ ከመፍጠር ባለፍ ማህበራዊ ትስስርን ለማጠናከር ትልቅ ሚና እንዳለው እንደ አቶ ኤፍሬም ይገልጻሉ፡፡

ከተማ አስተዳደሩ ችግሩን በመረዳት

ለችግር ለተጋለጡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በአዲሱ በጀት ዓመት 100 ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት 100 ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ መታቀዱን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጄ ዱጉማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ 400 ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ህክምና እንዲሰጡ ህንፃ ተገንብቷል። ከዚህ ውስጥ 125 ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ 100 ጤና ጣቢያዎች የቀዶ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል ያሉት ዶክተር ደረጄ፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት ጤና ጣቢያዎች በቅርበት የቀዶ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ሰፊ ሥራዎች ይሰራሉ ብለዋል።

በጤና ጣቢያዎቹ የሚሰጠው የቀዶ ህክምና አገልግሎት እናቶችን ማዋለድ፣ ትርፍ አንጀት፣ የታጠፈ አንጀት የማስተካከል እና ሌሎችንም



ዶክተር ደረጄ ዱጉማ

የህመም አይነቶችን ይጨምራል ያሉት ዶክተር ደረጄ፤ ይህ ማለት ጤና ጣቢያዎች ሁሉንም የቀዶ ህክምና አገልግሎቶች ይሰጣሉ ማለት ሳይሆን አቅማቸውን መሰረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ይህም ጊዜ ለማይሰጡ ህመሞች ፈጣን ህክምና ለማድረግ እና ወደ ሆስፒታል መሄድ ለማይችሉ ሰዎች እፎይታን የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ደረጄ ገለፃ፤ አሁን ላይ ጤና ጣቢያዎቹ የጤና ባለሙያ እና የመሳሪያ አቅርቦት ለማሟላት ርብርብ እየተደረገ ሲሆን፤ የህክምና አገልግሎት ግብዓት ሲሟላ ወደ ስራ ይገባሉ። ጤና ጣቢያዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ስራ በመጀመራቸው በገጠሩ እና ከከተማ ዙሪያ ወደ ከተማ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚንገላቱት እናቶች ቁጥር መቀነስ ችሏል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የጤና ጣቢያዎቹን አቅም ለማሻሻል እየሰራ ሲሆን፤ በሀገሪቱ የጤና ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ከዓለም አቀፍ እና አጋር አካላት ጋር በመተባበር ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል። ይህም በ2017 በጀት ዓመት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።



በይርጋዓለም ከተማ አስተዳደር፣ ፍልውሃ ክፍለ ከተማ ቱሳ ቀበሌ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆኑ ነዋሪዎች፤

# በክልሉ 360ሺህ ሕዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆኗል

**ሶሎሞን በየነ**

ሃዋሳ፡- በሲዳማ ክልል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 360 ሺህ ሕዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መሆኑ ተገለጸ።

የቢሮው ኃላፊ ከበደ ጋኖሌ (ኢንጅነር) በክልሉ የሥራ ምልከታ ላደረጉ የጋዜጠኞች ቡድን እንደገለጹት፤ የዛሬ አራት ዓመት ሲዳማ እንደ ክልል ሲቋቋም የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑ 38 ነጥብ 2 በመቶ ነበር። ይህም የሚያሳየው አብዛኛው ሕዝብ በንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ውስጥ እንደነበር ነው።

ክልል ከሆነ ወዲህ ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመት ውስጥ ችግሩን ለመቅረፍ በቁርጠኝነት በተሠራው ሥራ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑን ከ38 ነጥብ 2 በመቶ ወደ 60 በመቶ በእጥፍ ማሳደግ ትችሏል ብለዋል።

ከክልልነት በኋላ በተፈጠረው ምቹ አስተዳደራዊ መዋቅር በከፍተኛ ትኩረት ከተሠሩ መሠረተ ልማቶች ውስጥ አንደኛው ንጹህ የመጠጥ ውሃ የማስፋፋትና ተደራሽ የማድረግ ጉዳይ ነው የሚሉት ኃላፊው፤ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻር ብዙ ተዋናዮች አሉ። እነዚህን አካላት በማቀናጀትና በማስተባበር ቅድሚያ ችግሩ በጥልቀት የሚስተዋልባቸው ቦታዎች ላይ የውሃ ፕሮጀክቶች በስፋት መሠራቱን ተናግረዋል።

የቢሮው ኃላፊ ከበደ (ኢንጅነር) 875 መካከለኛ፣ አነስተኛ እና ጥቃቅን የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመት ውስጥ ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ ለአብነት ከጥቃቅኖቹ ውጭ በከፍተኛ መጠን የህብረተሰቡን የንጹህ መጠጥ ውሃ ጥያቄ የሚመልሱ 38 ወሳኝ የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች መከናወናቸውን አመላክተዋል።

38ቱ ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው 25 ሚሊዮን ብር እስከ ከ376 ሚሊዮን ድረስ የግንባታ ወጪ የሚጠይቁ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በድምሩ የ38ቱ ፕሮጀክቶች የግንባታ ውል ሁለት ቢሊዮን ብር ነው። ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ግንባታውን ለሚያከናውኑ ተቋራጮች የተከፈለ ሲሆን፤ ቀሪው ፕሮጀክቶቹ ሙሉ ለሙሉ እስኪጠናቀቁ ድረስ ይፈጸማል ብለዋል።

ከ38ቱ አንኳር ፕሮጀክቶች ውስጥ 28ቱ ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ኃላፊው ገልጸው፤ እነዚህ አንኳርና ሌሎች ጥቃቅን ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠታቸው ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ 650 ሺህ 840 የማህበረሰብ ክፍል የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 360 ሺህ ሕዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆኗል የሚሉት ኃላፊው፤ ክልል ከመሆኑ በፊት የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚው ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ነበር። ክልል ከሆነ በኋላ በተሠራው ሥራ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሕዝብ ቁጥሩን ወደ ሦስት ሚሊዮን ገደማ ማድረስ መቻሉን ተናግረዋል።

በዚህም በአጭር ጊዜ ውስጥ በተሠራው ሥራ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑን ከ38 ነጥብ 2 በመቶ ወደ 60 በመቶ በእጥፍ ማሳደግ መቻሉን የሚናገሩት ኃላፊው፤ በግንባታ ላይ ያሉት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ እንዲሁም በቀጣይ ለመሥራት በዕቅድ የተያዙት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ሲገቡ፤ በቅርቡ በክልሉ የንጹህ ውሃ መጠጥ ሽፋን 75 እና 80 በመቶ እንደሚደርስ አስገንዝበዋል።



ፋሪስ ደሊል(ዶ/ር)

# ዩኒቨርሲቲው ከ44ሺህ በላይ የቡና ችግኞች ለአርሶ አደሮች አሰራጨ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ክረምት የሚተከሉ ከ44ሺህ በላይ የቡና ችግኞች አዘጋጅቶ ለአርሶ አደሮች ማሰራጨቱን የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፋሪስ ደሊል(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በአራት የችግኝ ጣቢያዎች በዘንድሮ ክረምት የሚተከሉ ከ44ሺህ በላይ የቡና ችግኞች አፍልቶ ለወረዳው ማህበረሰብ እያሰራጨ ይገኛል፡፡

ቡና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በመሆኑ አርሶ አደሩ የቡና ችግኞችን በኩታ ገጠም እንዲሁም በአግባቡ እንዲተክል ከጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያና ከወረዳዎች ጋር በመተባበር እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ይህም ለድጋፍና ክትትል አመቺ ነው ብለዋል፡፡

በተቀሩት ጣቢያዎች ለደን የሚውሉ፣ የአካባቢን መራቆት የሚከላከሉ እንዲሁም አድገው ለጣውላነት የሚውሉ ከ100ሺህ በላይ ሀገር በቀል ችግኞችን መዘጋጀታቸውንም ገልጸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ችግኝ መትከል ህይወት የማስቀጠል ጉዳይ መሆኑን በመረዳት የአረንጓዴ አሻራን በማሳረፍ ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ ፋሪስ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ዩኒቨርሲቲው በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በዚህም በግብርና ዘርፍ አርሶ አደሩ ተጠቃሚነት ለመጨመር የክህሎት ስልጠና እንዲሁም ምርትና ምርታማነቱን እንዲያድግ የሚረዱ በምርምር የተገኙ የሰብል ዝርያዎችን የማቅረብ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

በጤናው ዘርፍም ከከፊል ኦሮሚያ፣ የም ዞን ከጉራጌ ዞንና ከምሥራቅ ጉራጌ ዞን ለሚኖሩ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የህክምና አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲሰጥ የነበረው የአዕምሮ ህክምና አገልግሎት ዩኒቨርሲቲው መስጠት መጀመሩን አስረድተዋል፡፡

በትምህርት ዘርፍ የትምህርት ጥራት እንዲሻሻል አንዱ ሥርዓተ ትምህርትን ማሻሻል እንዳለበት ተወስኖ ቢገባም በትምህርት አመራሩና መምህራን በኩል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አለመሠራቱን አውስተው፤ ዩኒቨርሲቲው ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን ለአንድ ሺህ መምህራንና የትምህርት አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠቱን ገልጸዋል፡፡

የግብዓት እጥረት ላለባቸው ትምህርት ቤቶች የወንበርና ጥቁር ሰሌዳ የማሟላት፣ የማጣቀሻ መጽሐፍት የማቅረብ፣ ቤተ ሙከራዎችን የማደራጀት ሥራ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ አስተዋጾኦ አለው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የመማር ማስተማር ሥራው ውጤታማ እንዲሆን በልዩ በትኩረት የሠራ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል፡፡

ዜና



አቶ ሞቱማ ተመስገን

## 102 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች በገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሊሠማሩ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኢኮኖሚ ዞኑ እስካሁን 102 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ሊሠማሩ መሆኑን የገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ባለስልጣን አስታወቀ። 142 ሄክታር መሬት ለኢንቨስተሮች መተላለፉም ተገልጿል፡፡

የገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሞቱማ ተመስገን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የኢንቨስትመንት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ሲሆን፤ እስካሁን 102 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ተመዝግበዋል፡፡

በኢኮኖሚ ዞኑ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን የሚያስፋና ገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንቨስትመንቶችን ለመቀበል ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እስካሁን 102 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ የተለያዩ ባለሀብቶች ወደ ዞኑ ገብተው ለመስራት ተመዝግበዋል ብለዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ፍላጎቶች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ጨምሮ ከተባበሩት አረብ ኤሚሬትስና ቻይና እንደሚገኙበት ጠቅሰው፤ በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በግብርና ምርት ማቀነባበር፣ በሎጀስቲክ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ማሳየታቸውን ገልጸዋል፡፡

ልዩ ዞኑ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት መነቃቃት እየታየበት በመሆኑ መሰረተ ልማቶች እየተሟሉ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡

የመንገድ፣ የውሃ፣ መብራት እና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች በግንባታ ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ኢኮኖሚ ዞኑ አዋጭና በጥናት የተረጋገጠ ቦታ ላይ ማረፉን በመግለጽ፤ 555 ሄክታር ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት ዝግጁ ተደርጓል ብለዋል፡፡ 142 ሄክታር መሬት ለኢንቨስተሮች ማስተላለፍ መቻሉንም ተናግረዋል፡፡

በኢኮኖሚ ዞኑ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን በማቀነባበር ወደ ውጭ የመላክ ፍላጎት ያላቸው ኢንቨስተሮች መኖራቸውን የገለጹት አቶ ሞቱማ፤ በተለይም በኮንስትራክሽን ግብዓቶችን፣ ሴራሚክ፣ በኢንዱስትሪ ፓርክ ደረጃ ለመገንባት ፍላጎት ያሳዩ ባለሀብቶች በቅርቡ ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዷል ብለዋል፡፡

ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ትልቅ የኢንቨስትመንት ካፒታልን ለመሳብ፣ የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ተኪ ምርቶችን በማምረት ከውጪ የሚገቡትን ለመቀነስ፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጪ ምንዛሪን ማስገኘትን ጨምሮ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ሽግግር እንዲመጣና የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ከቀረጥ ነጻ የማስገባት ዕድልን ጨምሮ የተለያዩ ማበረታቻዎች እንደሚደረጉላቸውም ገልጸዋል፡፡

ገዳ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን በሞጆና በአዳማ ከተሞች መካከል በ24 ሺህ ሔክታር መሬት ላይ እየተገነባ ይገኛል።

# የሀገራዊ ምክክር አጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ እስከ መስከረም መጨረሻ ይጠናቀቃል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት እስከ መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ እንደሚጠናቀቅ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አረዓያ (ፕ/ር) ገለጹ።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአሥር ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የተጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት እስከ መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው።

የአማራና ትግራይ ክልሎችም አንጻራዊ ሰላም በተገኘበት አጋጣሚ ሁሉ ወደ አጀንዳ ልየታ ለመግባት ዝግጅት መደረጉን ፕሮፌሰር መስፍን አብራርተዋል።

በአንዳንድ ቦታዎች ያለው የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታ የተወሰነ ተጽዕኖ ቢያሳድርም በተጀመረባቸው ቦታዎች የአጀንዳ ማሰባሰቡ ሂደት በተገቢው ሁኔታ እየሄደ እንደሚገኝም ኮሚሽነሩ ተናግረዋል፡፡

የአጀንዳ ልየታው እስከ መስከረም መጨረሻ የገፋው አፋር ክልል በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ሙቀት እየገባ በመሆኑ ነው ብለዋል።

የኮሚሽኑ ዋና ተግባር አካታችና አሳታፊ የሆነ ሀገራዊ ምክክር ማካሄድ በመሆኑ የአካል ጉዳተኞች ጉባኤ አዘጋጅቷል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ለሁሉም ዜጎች የጋራ መድረክ እያመቻቸ ሀገራዊ መግባባት እንዲፈጠር እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን፤ የምክክሩ ዓላማ ከሕዝብ የተሰበሰቡ አጀንዳዎች ሁሉ በሚገባ ተለይተው በተመረጡ የሀገሪቱ ተወካዮች በኩል አስፈላጊውን ውይይት ተደርጎ ከመግባባት መድረስ መሆኑን አንስተዋል።

በምክክር ሂደቱ እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት የውጭም ሆነ የውስጥ ጣልቃ ገብነት አለመኖሩን የጠቀሱት ፕሮፌሰር መስፍን፤ ነገር ግን የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉ ወገኖች ወደ ሀገራዊ ምክክሩ አለመምጣታቸው የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው ሲሉ ገልጸዋል።



ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለጻ፤ በምክክሩ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ተወስዶ ከማንም ጣልቃ ገብነት ነጻ ተደርጓል።

ለአብነትም የየመንና የሱዳን ሀገራዊ ምክክሮች የመንግሥትና የሌሎች አካላት ጣልቃ ገብነት ስለነበረባቸው ፍሬ አልባ ሆነዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# “ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን እየሠራን ነው”

- ብሩክ ከድር (ዶ/ር)

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ወቅቱን የሚመጥኑ የስልጠና መስኮችን በመቅረጽና ቴክኖሎጂን በማለማመድ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን እየሰራን ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ኢንስቲትዩቱ ገበያና ክህሎት መር የሆነ ስልጠናን በተግባር በመደገፍ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ ጥራት ያለው ስልጠና ለመስጠት፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ፣ ቴክኖሎጂና ኢንተርፕራይዝ ለማልማት እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት በቁርጠኝነት እየሰራን ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ዓለም አዳዲስ የኢንዱስትሪና የቴክኖሎጂ ልምምድ ውስጥ እየገባ ነው፡፡ ኢትዮጵያም ይህን የሚመጥን የሰው ኃይል ያስፈልጋታል፡፡ በዚህም ወቅቱን የሚመጥኑ ስልጠናዎችን ለመቅረጽ ዝግጅት እየተደረገ ስለመሆኑ አስታውቀዋል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች ገበያና ክህሎት መር የሆነ የቴክኖሎጂ ልምምድ እንዲያደርጉ እየተሰራ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ጥራት ያለው ስልጠናን ለመስጠት እያደረገ ባለው ጥረትም የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን በመለ ሀገሪቱ ተደራሽ ለማድረግ በመስራቱ፣በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር ልማት በሠራቸው ሥራዎችም የISO 9001:2015 ዓለም አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘቱን አስታውቀዋል።

ኢንስቲትዩቱ የተሰጠው የእውቅና ሰርተፍኬት ኢንስቲትዩቱን ተወዳዳሪና ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ፣ አጋሮችን ለመሳብ፣ የውስጥ ሥራዎችን በጥራት ለመፈጸም የዘርፉን ተዋንያኖች ብቁ ለማድረግ እንዲሁም የያዛቸውን ተግባራት በጥራት ለመፈጸም እና በቀጣይ የተመረጡ የስልጠና መስኮችን የተሻለ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ ይረዳል ብለዋል።

ሰርተፍኬት ማግኘት ግብ ባለመሆኑ ተከታታይ ሥራዎችን መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን አምነን በመሥራት ኢንስቲትዩቱ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችና የሚያመርታቸውን ምርቶች በደንበኞች ተፈላጊ ማድረግ እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን ማስቀጠል ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሰርተፍኬሽን ዳይሬክተር አቶ አምሳሉ እንየው በበኩላቸው፤ ኢንስቲትዩቱ የሠራቸው ሥራዎች በተቀመጠው ዓለም አቀፍ መስፈርት ተገምግመው ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ የISO 9001:2015 ዓለም አቀፍ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል ብለዋል።

ሰርተፍኬቱ የሰው ኃይላቸውን ብቃት የሚጨምር፣ ሰልጣኞች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እና አሰራራቸውን ውጤታማ የሚያደርግ መሆኑን አመላክተዋል፡፡





# በክልሉ ጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከ28 ሚሊዮን በላይ ደረሰ

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በክልሉ ጤና መድን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከ28 ሚሊዮን በላይ መድረሱን የኦሮሚያ ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ከ5 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሰዎች የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሲስተር ትግስት ተፈሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር 28 ሚሊዮን 015 ሺህ 714 ደርሷል፡፡

አገልግሎቱ ስላለው ፋይዳ ግንዛቤ እንዲጨምር ንቅናቄ በማካሄድና አገልግሎት አሰጣጥን በማስተካከል በቀጣይ ቁጥሩን ወደ 29 ነጥብ 5 ሚሊዮን ለማድረስ የሚሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በጤና መድህን አገልግሎቱ የክልሉ አካባቢዎች ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ የተደረጉ መሆኑን ጠቅሰው፤ መክፈል የማይችሉ ከ900 ሺህ በላይ ዜጎች አገልግሎቱን በነፃ እንዲያገኙ መደረጉን አስረድተዋል፡፡ ለዚህም መንግሥት 574 ሚሊዮን በላይ ብር ድጎማ ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የፌዴራል ድጎማ ሳይጨምር አምስት ቢሊዮን 435 ሚሊዮን 867 ሺህ ብር ከክልሉና ወረዳዎች የተሰበሰበ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በክልሉ የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በተሰራው ሥራ በ2016 በጀት ዓመት አምስት ሚሊዮን 836 ሺህ አባወራዎች በአዲስ አባልነት መመዝገብ መቻሉንም አስታውቀዋል፡፡

በክልሉ በተፈጠረው የሰላም እጥረት ምክንያት ግንዛቤ ለማስጨበጥ መንቀሳቀስ መቸገር፣ የበጀት እጥረት፣ የመድኃኒት አቅርቦት እጥረት እና የዋጋ መጨመር በጤና መድህን የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ የሚፈጥሩ ተግዳሮቶች ናቸው ብለዋል።

የበጀት እጥረትን ለመፍታት የማህበረሰብ ተሳትፎ እንዲጨምር የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም የሚያጋጥመውን የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን ለመፍታትና የግዢ ሥርዓቱን ከማሳለጥ አንጻር የማህበረሰብ መድኃኒት ቤቶችን የማስፋፋት እና የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት የሀገር ውስጥ ምርቶችን መጠቀም እንዲቻል የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተግባር መሰራቱን ሲስተር ትግስት አስታውቀዋል፡፡

## አዲሱ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ በረከት ፍስሀ ጽዮን እንደሚሉት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የብር አቅምን ማዳከም ( ዲቫሉዌት) ሳይሆን ገበያን መሠረት ያደረገ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት ( ፍሎቲንግ) ነው የፈጠረው ይላሉ፡፡

የውጭ ምንዛሪ ተመን በገበያ የሚወሰንበት (ፍሎቲንግ ኤክስቼንጅ ሬት) ሥርዓት ያለ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ባንኮችና ደንበኞች በሚኖራቸው ስምምነት የውጭ ምንዛሪ ተመን የሚወሰን መሆኑን ይጠቅሳሉ። በዚህ ምክንያትም የገንዘብ ዋጋ ሊጨምር እንዲሁም ሊቀንስ የሚችል ሲሆን ከውጭ የሚገቡ እቃዎችም ዋጋቸው ተለዋዋጭ እንዲሆን እንደሚያደርግ ይገልጻሉ።

ይህም የራሱ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች ይኖሩታል የሚሉት አቶ በረከት፤የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው በገጠራማው አካባቢ የሚኖር እንደመሆኑ አብዛኛው የሚጠቀምባቸው ምርቶችን ራሱ ያመርታቸዋል፡፡ ሌላው ለግብአትነት የሚውሉ ግብአቶችን ከውጭ የሚቀበል ነው ይላሉ፡፡ ይህ በመሆኑ ማሻሻያው የሀገር ውስጥ ምርትን በማበረታታት ያለአግባብ ከውጭ የሚገቡ ግብአቶች በማስቀረት የዶላር ፍላጎትን ለመቀነስ እድል ሊፈጥር የሚችል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ይህም ሆኖ ሥርዓቱ የተወሰነ የገበያ ንረት የሚያመጣ ቢሆንም መንግሥት ያስቀመጠው አቅጣጫ ሲተገበር ማሻሻያው ከፍያለ ጉዳት አያስከትልም ይላሉ፡፡

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚ ትምህርት ክፍል መምህር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት ሰሞኑን የተደረገው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የገንዘብ ተመን በገበያ የሚወሰንበት (ፍሎቲንግ ) ወይስ የገንዘብ አቅም ማዳከም (ዲቫሉዌት) ነው በሚል አከራካሪ ነገሮች ቢነሱም የገንዘብ ተመን በገበያ የሚወሰንበት (የፍሎቲንግ) ሥርዓት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ዶ/ር ይንገስ ይህ ሥርዓት የተለያዩ ሀገራት ሲተገብሩት የቆየ ሲሆን፤ አንዳንዶቹን ውጤታማ ሲያደርግ አንዳንዶቹን ደግሞ መጉዳቱን ይገልጻሉ፡፡

በዚህ ሥርዓት በሀገር ውስጥ የሚኖረው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እጅጉን ወሳኝ መሆኑን የሚገልጹት መምህሩ፤ ታዳጊ ሀገራት ለውጭ ገበያ ከሚያቀርቡት ይልቅ ከውጭ የሚያስገቡት ሸቀጦች የሚበልጡ በመሆኑ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደሚያጋጥማቸው እሙን ነው ይላሉ፡፡ ኢትዮጵያም ይህ እንደሚገጥማት ግልጽ መሆኑና ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ያገኘችው ድጋፍና ብድር ችግሩን ለመቋቋም የሚያግዛት መሆኑን አንስተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜም ሀገሪቱ ያገኘችው ድጋፍና ብድር ምን ላይ ታውለዋለች የሚለው ጉዳይ ለሥርዓቱ ውጤታማነት ወሳኝ በመሆኑ ለኢንቨስትመንትና የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት ማዋል ከቻለች ሥርዓቱ መልካም ነገሮችን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ሕዝቡ መሠረታዊ ከሆኑ ነገሮች ውጪ የውጭ ምርቶችን ባለመግዛትና የሀገር ውስጥ ምርቶችን የመጠቀም ባህሉ እያደገ ከሄደ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ውጤታማ ሊሆን ይችላል ነው የሚሉት፡፡

በአንድ ሀገር የኢኮኖሚ የእድገት ውስጥ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ምርት መጠን ወሳኝ ነው ያሉት መምህሩ፤ ለዚህ ሥርዓት ውጤታማነት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን አይነትና ብዛት መጨመርና ከውጭ የሚገባውን ዕቃዎች መቀነስ እንደሚያስፈልግ ነው ያብራሩት፡፡

በፍሎቲንግ ሥርዓት ውስጥ ሌላኛው ጥቅም ጥቁር ገበያና መደበኛው ገበያ ላይ የሚኖረው ልዩነት እንዲጠብ እድል የሚፈጥር መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ማሻሻያው ለተለያዩ የውጭ ሀገራት ባለሀብቶች የበለጠ ማራኪ እንደሚያደርጋት ነው የተገለጸው፡፡ይህም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት እንዲያስመዘግብ፣ የራስን ምርት የመጠቀም ባህል በማዳበር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በዘላቂነት የሚያሳድግ መሆኑ ተገልጿል፡፡

## የኢንሹራንስ ዘርፉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያስፈልጋል፡፡ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት የኢንሹራንስ ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚገባውን ድርሻ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል ነው የሚሉት፡፡

አቶ በለጠ፤ ኢንዱስትሪው በሌላው ሀገር እንደሚታየው ዓይነት ለውጥና ዕድገት እንዲያመጣ የፖሊሲ ውሳኔዎች ያስፈልጉታል ሲሉም አክለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ሰጪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ያሬድ ሞላ፤ በሌሎች ዓለም ሀገራት የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪው እራሱን የቻለ ኮሚሽን ወይም ተቆጣጣሪ ባለስልጣን አለው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪው ከባንኮች ጋር በመሆን በብሄራዊ ባንክ ስር ነው የሚተዳደረው፡፡ ይህም ለዘርፉ እድገት እንቅፋት በመሆኑ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ፍቃድ እንዲሰጠው ማህበራችን ለብሄራዊ ባንክ ጥያቄ አቅርቧል ይላሉ፡፡

ብሄራዊ ባንክም ጥያቄያቸውን ተቀብሎ የዓለም ባንክና የውጭ ባለሙያዎችን ያቀፈ ቡድን በማዋቀር ገለልተኛ የኢንሹራንስ ተቆጣጣሪ እንዲቋቋም መወሰኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የሽግግር ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነና ከአንድ ዓመት በኋላ አሰራሩ ተግባራዊ እንደሚደረግ ይናገራሉ፡፡

ውሳኔው ወደስራ ሲገባም ለተገልጋዩ ማህበረሰብ፣ ለሙያተኞችና ለአጠቃላይ ዘርፉ መሻሻል ትልቅ ዕድል እንደሚፈጥር ይገልጻሉ፡፡

እንደ አቶ ያሬድ ገለጻ፤ ኢንሹራንስ በባህሪው ዓለም አቀፋዊ በመሆኑና የውጭ ኩባንያዎች ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸው የቴክኖሎጂ፣ የአሰራርና የእውቀት ሽግግር ስለሚፈጥር ማህበሩ የኢንሹራንስ ዘርፉ ለውጭ ገበያዎች እንዲከፈትም ለብሄራዊ ባንክ ጥያቄ አቅርቧል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ዜጎች እየተጎዱ በመሆኑ ዜጎችም የኢንሹራንስ ጥቅሙ ገብቷቸው እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በኢትዮጵያ የንብረት ኢንሹራንስ ላይ ጥሩ እየተሰራበት ቢሆንም በህይወት ኢንሹራንስ ረገድ በስርጭቱና በአገልግሎቱ ላይ በበቂ ሁኔታ አለመሰራቱን ያነሳሉ፡፡

ኢንሹራንስን ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ከተለያዩ የትምህርት መስኮች ጋር ቀላቅለው ቢያስተምሩም በተፈጥሮው የተለየ ሙያ በመሆኑ የራሱ ክህሎትና እውቀት ስለሚጠይቅ፣ በኢትዮጵያ በኢንሹራንስ ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚስተዋል ፕሬዝዳንቱ ይገልጻሉ፡፡

ችግሩን ለመፍታት ማህበሩ ከብሩህ ፋይናንስ ጋር በመሆን ከሁሉም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተወጣጡ ባለሙያዎችን መልምሎ በማሰልጠን ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት እያደረገ ይገኛል የሚሉት አቶ ያሬድ፤ ትምህርቱ በኢትዮጵያ መጀመሩ ብቃት ያላቸውን ሙያተኞች በማፍራት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለዜጎች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ እንደሚያስችል ይናገራሉ፡፡

የብሩህ ፋይናንስ መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ጌታቸው በሻወርድ በበኩላቸው፤ በዘርፉ እየታየ ያለውን የተማረ የሰው ሀይል እጥረት ለመፍታት በኢንሹራንስና በባንኩ ዘርፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ እየተሰራ ነው ይላሉ።

በዚህም ተቋማቸው በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለንደን ከሚገኘው ቻርተር ኢንሹራንስ ኢንስቲትዩትና ከኢትዮጵያ መድን ሰጭዎች ማህበር ጋር በመተባበር በቅርቡ በኢንሹራንስ ሴርተፊኬት 79 ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ማስመረቁን አስታውሰው፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሁሉም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተወጣጡ 50 ሰልጣኞችን በዲፕሎማ መርሀ ግብር ተቀብሎ ማስተማር መጀመሩን ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ በኢንሹራንስ ዲፕሎማ ያላቸው ባለሙያዎች ቁጥር 46 ብቻ መሆኑንና የተጀመረው መርሃ ግብር የባለሙያዎቹን ቁጥሩን በእጥፍ እንደሚያሳድገው የሚገልጹት አቶ ጌታቸው፤ ሙያተኞችን በውጭ ሀገራት ልኮ ለማስተማር ከጊዜና ከገንዘብ አንጻር ከባድ በመሆኑ የአለም ዓቀፉን መመዘኛ በማሟላት ለኢትዮጵያ በሚያመች መልኩ ትምህርቱ እየተሰጠ ይገኛል ነው ያሉት፡፡

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ በቀጣይ በኢንሹራንስ ዘርፉ ላይ በኢትዮጵያ የሌሉ የተለያዩ የትምህርት መስኮችን ለመክፈት የታቀደ ሲሆን፤ ትምህርቱን በድሬዳዋ፣ በሀዋሳና በሌሎችም የክልል ከተሞች የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡ እንዲሁም ሰልጣኞቹን ወደ ተለያዩ ሀገራት በመውሰድ የስራ ላይ ልምድ እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

የኢንሹራንስ ዘርፉ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል እያገኘ ከሄደና ተራማጅ በሆኑ ፖሊሲዎች ከተደገፈ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገቱ የሚኖረው ድርሻ እየተሻሻለ ይሄዳል፡፡

## ለችግር ለተጋለጡ ወገኖች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲሁም ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ከከተማው ነዋሪ፣ ከባለሀብትና ከተለያዩ ተቋማት እንዲሁም ለጋሽ አካላትን በማስተባበር ሀብት በማሰባሰብ በየአካባቢው በችግሩ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ካለባቸው የኑሮ ጫና ለማቃለል እየሰራ እንደሚገኝ ያብራራሉ፡፡

በተለይ ጽህፈት ቤቱ ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚረዱ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ተሞክሮችን መነሻ ያደረገ ጥናት ማድረጉን አውስተው በቀጣይ በከንቲባ ጽህፈት ቤት አጸድቆ በ2017 በጀት ዓመት በከተማዋ የሚገኘውን ሀብት በመሰብሰብ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለመሆን ማቀዱን አመላክተዋል፡፡

በዚህም በ2016 በጀት ዓመት በገንዘብ፣ በፕሮጀክት፣ በአገልግሎትና በአይነት ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት በመሰብሰብ ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

ጽሕፈት ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ኢንስቲትዩት የጥናትና ማማከር ባለሙያ የሆኑት ዮሐንስ ጴጥሮስ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በሀገር እድገት ላይ ትልቁ ሃብት የሰው ሃይል በመሆኑ የማህበረሰብ ጥበቃ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባው ይናገራሉ፡፡

ጽህፈት ቤቱ እስካሁን ባከናወናቸው ተግባራት ምን ውጤት አመጣ? ምንስ ተግዳሮት ገጠመው በሚል ጥናት ማድረጋቸውን የሚናገሩት ዮሐንስ(ዶ/ር)፤ በጥናቱ መሰረት የከተማ አስተዳደሩ ማህበራዊ ትረስት ፈንድ በሚያደርገው እንቅስቃሴዎች ዜጎች በዘላቂነት እንዲቋቋሙ በማስቻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል ብለዋል፡፡

በችግር ወቅት የመደጋገፍ እሴቶችን ማጠናከር እንደሚገባ የተደረገው ጥናት ቢያመላክትም በሌላ በኩል ይህን ማሳለጥ የሚችል አሠራር ያለመዘርጋት፤ ዜጎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንጻር ድክመት መኖር፣ ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ ከማድረግ አኳያ ክፍተቶች መኖራቸውን ጥናቱ እንደሚያስረዳ ገልጸዋል፡፡

በከተማዋ የሚኖሩ ለችግር የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚ ውስጥ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት ዮሐንስ(ዶ/ር)፤ ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ከተቻለ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ስራ መስራት በቀጣይ ሰፊ ሀብት ማሰባሰብ እንደሚቻል ጥናቱ ያስረዳል ብለዋል፡፡

እንደ ዮሐንስ(ዶ/ር) ገለጻ ጽህፈት ቤቱ ከባለድርሻ አካላት የሚያገኘውን ሀብት ለማህበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሰለባ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የህግ ማዕቀፎችን በተከተለ መንገድ ማስተላለፍ ይገባል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ትረስት ፈንድ በ2011 ዓ.ም የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ሲሆን ዓላማውም ገንዘብ በማሰባሰብ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የከተማው ነዋሪዎችን በዘላቂነት ማቋቋም እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ይህ ተቋም በከተማዋ ለሚገኙ በችግር ለተጋለጡ ወገኖች ፈጥኖ ደራሽ ሆኖ ከችግር የሚያወጣ ግዙፍ ተቋም

# ርዕሰ አንቀፅ

## የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱ ተስፋዎች!

በኢትዮጵያ ከሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ሥራዎች መካከል በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሚካሄደው ይጠቀሳል። ይህ ኢንቨስትመንት በውጭ ኩባንያዎች የሚካሄድ እንደመሆኑ ይዞት የሚመጣው ካፒታል ወይም የውጭ ምንዛሪ፣ ቴክኖሎጂና በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላለ በብልጽግና ጎዳና ላይ የሀገር እውቀት በእጅጉ ይፈለጋል።፡

እንደ ቻይና ያሉት ያደጉት ሀገሮች ጭምር በእጅጉ የሚፈልጉትን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ፋይዳ የኢትዮጵያ መንግሥታትም በሚገባ በመገንዘብ ለኢንቨስትመንቱ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ ጥረት አድርገዋል። ዘርፉን አላላውስ ሲሉ የቆዩትን ችግሮች ለመፍታትም ያላሻሻሉት አሠራር የለም ማለት ይቻላል።

ፈተናዎቹ ከባድ ቢሆኑም በዘርፉ ብዙ ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶችን በመሳብ፣ ባለሀብቶቹ የወጪ ምርቶችን እያመረቱ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኙ የተደረጉባቸው ሁኔታዎች ታይተዋል።

የለውጡ መንግሥትም ይህን ለውጥ ባለፉት ስድስት ዓመታት ለማስቀጠል ብዙ ጥረት አድርጓል። እንደ ሰላም እጦት ላሉ ተግዳሮቶች በባህሪው ድንጉጥ ለሆነው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ያለፉት የኢትዮጵያ ዓመታት ምቹ ሊሆኑ እንደማይችሉ ይታመናል።

በኮቪድ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነትና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በታዩ ግጭቶች ፣ በዓለም አቀፍ ተቋማትና በምእራባውያኑ ያደጉት ሀገሮች ጫናዎች እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ስትፈተን የቆየችው ኢትዮጵያ፣ እነዚህን ፈተናዎች እንደ መልካም አጋጣሚ ጭምር በመጠቀም በተለያዩ ዘርፎች ለውጦችን አስመዝግባለች።

በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትም ዘርፍ ቢሆን ለውጦች አሳይታለች። ሀገሪቱ እንደ ሀገር ብቻም ሳይሆን እንደ ክፍለ አህጉርና አህጉርም በዘርፉ ያሳየቻቸው ለውጦችም ይህንኑ ያመለክታሉ።

ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃዎች መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው፤ መረጃዎቹ እንደጠቆሙት፤ በ2016 በጀት ዓመት ሦስት ነጥብ 82 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል። ይህም የዕቅዱን 80 በመቶ ያህል ነው፤ ይህ አፈጻጸም ከቀደመው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ የ11 ነጥብ አምስት በመቶ ጭማሪም አለው። አፈጻጸሙም ከ2014 ወዲህ የተመዘገበው ትልቁ ውጤት ተብሏል።

ለውጦቹ በሀገር ደረጃ ብቻ የሚጠቀሱ አይደሉም፤ ሀገሪቱ ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት በሳበችው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚዋ ሀገር መሆን ችላለች። የዓለም ኢንቨስትመንት ሪፖርት መረጃን ዋቢ ያደረጉ ምንጮችም ይህንኑ አረጋግጠዋል። ለኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ የሚችሉትን ኬንያንና ኡጋንዳን ልቃ በመገኘትም በክፍለ አህጉሩ ፊት ለፊት ላይ መቀመጥ ችላለች።

ሀገሪቱ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመነት የምታስመዘግበው ለውጥ እንደሚቀጥል መረጃዎች ያመለክታሉ። በ2017 በጀት ዓመት አራት ነጥብ 52 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ከታቀደበት ሁኔታም መረዳት ይህንኑ መገንዘብ ይቻላል።

በሀገሪቱ ባለፈው በጀት ዓመት የተከናወኑ ተግባሮችም በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እያስመዘገበች ያለችውን ውጤት ማስቀጠል እንደምትችል ያመላክታሉ። ከተለያዩ ሀገሮች ከመጡ የኢንቨስትመንት አካላትና ባለሀብቶች ጋር የተደረጉ ውይይቶችና ይህን ተከትሎ ባለሀብቶች በሀገሪቱ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ ያሳዩት ፍላጎት ከፍተኛ እየሆነ ያለበት ሁኔታ እንዲሁም አዳዲስ ሀገራት በዘርፉ ለመሰማራት ያሳዩት ፍላጎት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቱ እንደሚጨምር ይጠቁማሉ።

የውጭ ባለሀብቶች በጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ የሚያስችል አዋጅ ማውጣቱ፣ የውጭ ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠሩ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ፣ ወደ ሥራ የገባው የካፒታል ገበያ ለውጭ ባለሀብቶች ጭምር ክፍት መሆኑ፣ ሌሎች ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች እንደመሆናቸው ዘርፉ በቀጣይ ብዙ ለውጥ የሚመዘገብበት ይሆናል ብሎ መገመት ይቻላል።

ሰሞኑን ወደ ትግበራ የገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያና እሱን ተከትሎ ብሄራዊ ባንክ ያወጣው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያም በተለይ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱ መጨመር ያላቸው ሚና ከፍተኛ ስለመሆኑ በመንግሥትም በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችም እየተጠቀሰ ይገኛል።

ማሻሻያው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመልሱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፤ ማሻሻያው መውጣቱን ተከትሎ ሀገሪቱ ለልማቷ በእጅጉ የሚያስፈልጋትን ብድር ማግኘት ያስቻላት ሆኗል። የእነዚህ ተቋማት ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ ማዞር የውጭ ባለሀብቶችና ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች ኢትዮጵያን ምርጫቸው እንዲያደርጉ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያሳርፍ ይችላል።

ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሚሆኑ ምቹ ከባቢዎችን መፍጠር እንደታቻለና በዚህም ለውጥ ማምጣት እንደተጀመረ ሁሉ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱን ይበልጥ ለመሳብ የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎች ዘላቂነት ባለው መልኩ በማስተዋወቅ ላይ መሰራት ይኖርበታል።

ባለሀብቶቹ ዘርፉን ለመቀላቀል ሲመጡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ፣ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች መሳብ መቻል፣ ኢንቨስትመንቱ ከቁጥር ባሻገር ውጤታማ በሚሆንበት ላይ በትኩረት መስራት በቀጣይ በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለምለም እንጀራ እንጂ ለምለም የድንግልና ተስፋ እየበላን አንኑር!!

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ማንኛችንም የማንክደው ዓለም ሁሉ የሚመሰክረው አንድ እውነታ አለ። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከማንም በላይ የአንጡራ ሀብት ባለቤት ናት። ከኛ ልጆቿ በስተቀር ክብሯን ማንም ያልነካው ባለግርማ እመቤት ናት። የ3 ሺህ ዘመናት ታሪክ ያላት ወርቃማ ባለታሪክ ናት።

ከምንም በላይ ደግሞ ሁሉም የሚመኟትና የሚጎመዧት ድንግል ንግሥት ናት። ገና ምኑም ያልተነካ አንጡራ ሀብት፣ እግዜር እንደፈጠረው ቁጭ ያለ ድንግልና፣ የሚመለከቷት እንጂ የማይገቡባት ገነት፣ የሚመጻደቁባት እንጂ የማይጸድቁባት መቅደስ፣ የሚኖሩባት እንጂ የማያኖሯት እርስት ላይ ነን።

የወደቁት ተነስተው በእግራቸው ቆሙ። ኋለኞችም ተስፈንጥረው ፊተኞች ሆኑ። የሞቱት መቃብር እንኳን ሳር አብቅሎ ለመለመ። ተርበው የጫማ መርገጫ የበሉም ዳቦ ማደል ጀመሩ። እኛ ግን የተፈጥሮ ድንግልናን ታቅፈን ህልም ስናይ 3 ሺህ ዘመን ባተ። ከሰው ዘር መጀመሪያ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ድንግልና ለምን? ፈጣሪ በምድር ባርኮ የሰጠንን፣ ብሉ ደግሞም አብሏት ያለንን በረከት ይዘን ስንዘምርለት ብቻ የምንኖረው ለሰማይ ቤት ወይንስ ከሩቅ ለሚመጣው ትውልድ አስበን?

ያለን የተሰጠን ኩራት ነበር። አላወቅንም፤ አልገባንም እንጂ አሁን ሀፍረት ነው የሆነብን። ዓለም ሁሉ የሚፈልጋትና የሚያውቅላትን ሀገር አሁን ግን ዓለም ሁሉ ቁልቁል የሚያያት ምስኪን ምንዱባን አድርገናታል። ማን? እኔ፣ አንተ፣ አንቺ፣ ሁላችንም። ሁሌም ግን የምንለው "እነርሱ!...እሷና እሱ" ነው። "እነርሱ" የምንለው ማንን ነው? እነርሱስ እነማን ናቸው? "እነ እገሌ እኮ ጥሩ ሠርተው ነበር፤ እነ እንቶኔ ግን ይህችን ሀገር ቀበሯት" የምንለው የለንም።

የምናወራው ስለ 3ሺህ ዘመን ድንግልና ነውና ሁላችንም ባለዕዳዎች ነን። "ኢትዮጵያ ማለት እኮ አፈሯ ገራገር፣ ምድሯም ለምለም ነው" እንላለን። ግን አፈራቸው ደረቅ፣ በድንጋይ ላይ የሚኖሩት እነዚያ የምናውቃቸው ሀገራት ዛሬ የት ደርሰዋል? "ሀገራችን በጠላት ያልተወረረች፣ ዓለምን ሁሉ ያንቀጠቀጠች እኮ ናት" እንላለን እንሸልላለን።

ግን በጠላቶቻቸው እግር ስር ወድቀው የተንቀጠቀጡ ዛሬ ያሉበትን ስንመለከት ከቶ አናፍርም ይሆን? በቀዝቃዛ የድንጋይ ዋሻ ውስጥ ተቀምጠን የድሮ አያቶቻችንን ጀብዱና ለተራበው እንጀራና ዳቦ የለገስንበትን ዘመን ስናወሳ ሰውነታችን ከቶ ስለምንስ አይሳቀቅም?

ታሪክ አናውራ፣ በነበረንም አንኩራ አይደለም። ካላከልንበት እነርሱንም እጀ ሰባራ አመድ አፋሽ እናደርጋለን። ቀጣይ ለኛም የሚወራልንን የራሳችንን ታሪክ መሥራት አለብን። ስንሠራ ስለአሁንም ሆነ ስለድሮው የሚያወራልን ብዙ ነው። ሁላችንም በአፈ ታሪክም ሆነ ከብራናና ከመሰል መዛግብቶች ላይ ስንሰማው የኖርነው ነገር አለ።

"ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ማዕድናት የተከበበችና የበለጸገች ናት። የእኚህንም መገኛ የሚያውቁና በአደራ ተቀብለው በምስጢራዊ መንገድ ከትውልድ ትውልድ የሚያቀባብሉ የተመረጡ ሰዎችም አሉ" ለሚለው ማናችንም እንግዳ አይደለንም። ታዲያ እኛ እየተራብንና በችጋር እየተጠበስን ይህንን እውነት፣ ይህንን ድንግልና ደርሶ የሚበላው ትውልድ የትኛው ትውልድ ነው? ወይንስ እንደ ታቦት ጽላት በክብር ይዘን እስከ ምጽአት ቀን ልንጠብቅ ነው? ያልገባን፣ ያልተረዳነው አንድ ነገር ሳይኖር አይቀርም።

አለኝ አለኝ ማለት ብቻ ዋጋ ቢስ ነው። "ኩራት እራት አይሆንም" እንደምንለው ሁሉ ጽድቅ የሌለበት የድንግልና ዝማሬ ኩነኔ ነው። ስብከት አይሁንና በቅዱስ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኝን አንድ ታሪክ ያስታውሰናል። አንድ ጠቢብ ለገበሬዎቹ ለእያንዳንዳቸው እንቁ ፍሬ ሰጣቸው። በለምለም መሬት ላይ የዘራውም ፍሬው መቶና ሃምሳ ብዙ እጥፍ አፈራለት። ጠቢቡ መጥቶ በተመለከተ ጊዜም እጅግ አመሰገነው።

ቀሪዎቹን እንዝላልና ወደ መጨረሻው ሰው መጣና ፍሬውን ከወዴት አኖርከው? ባለው ጊዜም ቃል በቃል ባይሆንም እንዲህ ነበር የመለሰው "ጌታዬ! የሰጠኸኝን ሌባ እንዳይሰርቀኝና እንዳይበላሽ አድርጌ በታማኝነት አኑሬልሀለሁና እንካ" ሲል ያቺኑ አንድ ፍሬ መልሶ ሰጠው። የኛም ነገርና የሀገራችን ድንግልና ልክ እንደዚሁ ታሪክ ነው። የሰጠን እንድንሰራበት፣ ፍሬ አፍርቶ ብዙ እጥፍ እንዲሆን እንጂ በአደራ ይዘን እንደተሰጠን ሳንነካው ደብቀን እንድናኖረው አይደለም። ሀገራዊና ምስጢራዊ ሀብት ይዘን የምንቀባበልም ብንኖር በመጨረሻው ስንጠየቅበት እንዲሁ ነው።

ለኢትዮጵያ ከኢትዮጵያዊ ሌላ ማንም የላትም። ገራገሩን አፈሯን አርሰን ካልዘራን፣ አዝመራውን ካላጨድን፣ ወቅተን ጎተራውን ካልሞላን የልምላሜ መዝሙራችን ከንቱ ነው። ከገበሬ ገበሬ፣ ከጠቢብ ጠቢብ፣ ከምሁር ምሁር አለን። ሁሉንም የዚህችን ሀገር ጣጣ ገበሬው ላይ ጥለን ቀሪ አብዛኛዎቻችን ግን አውሮፓና አሜሪካ ነን። ዛሬ ላይ የት አለ ምሁሩ? የትነው ሳይንቲስቱ? ወዴት ነው ዶክተሩ? ብለን ብንፈልግ የአብዛኛዎቹ መገኛ ከዚያ ያላለፈ ነው። ዕውቀትና ጥበባችንን የምንጠቀምበት ሀገራችንን ለማበልጸግ ሳይሆን ከሀገራችን ሸሽተን ለማምለጥ ነው።

በስኮላር ሺፕ የበለጠ ዕውቀትና ክህሎት አዳብረን ለዚህች ሀገር ስንታሰብ አብዛኛዎቻችን ግን ቀልጠን እንቀራለን። ሀገር ወክለን ለስፖርት ሄደን እንኳን በዚያው እንጠፋለን። "ኑሮን ለማሸነፍ፣ ፖለቲካን በመጸየፍ..." እያልን ራሳችንና ሕዝባችንን እናሞኛለን። ናሳን ጨምሮ ዓለማችን ላይ አሉ በተባሉ ግዙፍ የምርምርና የቴክኖሎጂ ማዕከላትና በተለያዩ ትላልቅ ተቋማት ውስጥ ኢትዮጵያውያንን ማግኘት የሚያስገርም አይደለም።

ለየባዕድ ሀገሩ ተአምራትን እንሠራለን። ጠንቋይ ግን ለራሱ አያውቅም። ሀብታሙም ድሀውም፣ የተማረም ያልተማረም፣ ፕሮፌሰር ነጋዴውም ሁላችንም ኑሮ ከብዶን ከሀገር ከወጣን፣ ሁላችንም ፖለቲካን ፈርተን እግሬ አውጪኝ ካልን፣ ታዲያ ማነው ለዚህች ሀገር በመስዋዕትነት የተፈረደበት? ሁሉም ራሱን ከደሙ አንጽቶ ገለል ሲል ማንስ ለብቻው የበላው ዕዳ አለበትና እዚህ ቁጭ ብሎ ለሀገሩ ሻማ ይሆናል? በሀገርህ ስለሀገርህ ኑር ተብሎ የገዘቱትም ሆነ ያስማሉት ማንም የለም። እያንዳንዳችን፣ ሁላችንም ተጠያቂ ባለአደራዎች ነን።

ቢመቸውና ቢቀናው ሁሉም ሰው ከአውሮፓና አሜሪካ ደርሶ የሚያስገባው ስለት ካለበት የዚህችን ሀገር የድንግልና ዳቦ ቆርሶ የሚያበላት ማነው? እዚህ ሀገራችን ውስጥ የተቀመጥንስ ዕድሉን ባለማግኘታችን አማራጭ ስላጣን ነውን? ከሆነስ ብንኖርም የለንም። ሌላኛው ያልተገረሰሰ ድንግልናችንም ባዕድ ናፋቂነታችን ነው። አንውጣ አንሥራ አይደለም፤ የትም ዓለም ያለ ነውና። ነገር ግን ያለንን ይዘን እንደወጣን ቀርተን፣ እንደወጣን አንሙት።

ሀብታም ሀገር አለችን። ውብና ድንግል እናት አለችን። ግን አልሠራንባትም፤ አልሠራንላትም። አልበላንም፤ አላበላናትም። የምንኖረው የተሰጠንን ህይወት አይደለም። ማስተዋል ካቃተን ውቧን ድንግል ሀገር የኮሰሰች አሮጊት አድርገን፣ ወርቋን እንደ ድንጋይ ተንተርሰን እንኖራለን። የኛ ችግር ችግራችንን የምንመለከትበት መንጽርም ጭምር ነው። ተጠላልፈን ከወደቅንበት ተሠርተንና ሠርተን ለመነሳት ስንችል ስለወደቅንበትና ስለቆምንበት የኋላ ዘመን እያነሳን እንወድቃለን።

እኔ እንዲህ አደረኩና ለሀገሪቱ ምንስ ልፈጠር... አንበል። ምክንያቱም ሁሉም እንዲህ ነው የሚለው። እንዲህ እያለ ነው ከኃላፊነቱ የሚሸሸው። በሀገራችን ለሀገራችን ብቻ ሠርተን፣ አበልጽገን መበልጸግ ስንችል ቁራሽ እንጀራ ፍለጋ ባዕድ ለባዕድ፣ በረሀ ለበረሀ እንዋትታለን። እስከመቼ ማንን እንጠብቅ? ለምለም እንጀራ እንጂ ለምለም የድንግልና ተስፋ እየበላን ብቻ አንኑር!!

# ተጠየቅ

## “ከ20 ሺህ ሕንጻዎች የእሳት መከላከያ የደህንነት መስፈርቱን አሟልተው እውቅና የተሰጣቸው 43ቱ ብቻ ናቸው”

- አቶ ይከፈለው ወልደመስቀል

የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር

በሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ

**አዲስ አበባ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገች የመጣች ከተማ ናት። ዘመናዊ ሕንጻዎች፣ ሆቴሎች፣ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች በርካታ ፋብሪካዎች አቅፋ ይዛለች። እነዚህ ተቋማት ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን አደጋን በመከላከልና በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሥራ ይጠበቅበታል። የዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን የከተማዋን ዕድገት የሚመጥን የአደጋ ቅድመ መከላከል፣ በመዲናዋ የሚደርሱ አደጋዎችን የመቆጣጠርና የመከላከል የዝግጁነት ደረጃ፣ አደጋ ከደረሰ በኋላ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ በምን መልኩ አደጋን የመከላከል ዝግጁነት ምን እንደሚመስል የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽን ኮሚሽነር ይከፈለው ወልደመስቀል ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ምንባብ!**

**አዲስ ዘመን፡- በበጀት ዓመቱ አደጋን ከመቀነስና ከመከላከል አኳያ ምን ታቅዶ ምን ተሰራ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** በኮሚሽናችን የሚከናወነው የአደጋ የመከላከል ሥራ ሶስት ደረጃዎች ያሉት ነው። የመጀመሪያው አደጋ ከመድረሱ በፊት ቀድሞ የአደጋ ስጋትን በማጥናት የማቅለያ ርምጃ እንዲወሰድ ለማህበረሰቡ የማስጠንቀቂያ መልዕክት እንዲደርስ ማድረግ ነው። ሁለተኛው አደጋ ከደረሰ በኋላ ምላሽ የመስጠት ሥራ ነው። በሶስተኛ ደግሞ በአደጋ የተጎዱ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ነው።

እኔ የምመራው የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ የአደጋ መከላከል ሥራ ብቻ የሚከናወንበት ነው። አደጋ ከመድረሱ በፊት ስጋቶችን በማጥናት አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ ርምጃዎች በተቋማት እንዲወሰዱ፣ በማህበረሰቡ ጥንቃቄ እንዲደረግ በእቅድ የማስተማር ሥራ ሰርተናል። በዚህ መሠረትም ከነበሩን ዋና ዋና እቅዶች አንዱና ዋነኛው ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት ነው። የግንዛቤ ሥራው በሕትመት ሚዲያው፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ ብሮሸሮች፣ እንዲሁም በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ሁሉን የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ዕለት ከዕለት በምንሰጠው መረጃና የማስጠንቀቂያ መልዕክቶች ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው ይሰራል።

አደጋ ሲያጋጥም ከአደጋው ህብረተሰቡ ሊማር በሚችልበት ደረጃ ዘገባዎችን በመሥራት ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ እና ጥቃቄ እንዲያደርግ ይደረጋል። ቤት ለቤት የማስተማር ሥራ እንሰራለን። በስልክ “ስቲከር” በመለጠፍ የተቋሙ አድራሻ እንዲኖራቸው እና አደጋን በመካከል ሂደት እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል። ከዚያ ውጭ በመድረክ ሌሎች ተቋማት በሚፈጥሯቸው የተለያዩ የውይይት መድረኮች ላይ በመገኘት የማስተማር ሥራ ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡- በኮሚሽኑ የሚሰራው የግንዛቤ ሥራ ማህበረሰቡ ስለ አደጋ ያለው ግንዛቤን ማሳደግ ተችሏል ብለው ያስባሉ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** የግንዛቤ ደረጃው አሁንም ገና ብዙ ሥራ መሥራትን የሚጠይቅ ነው። ማህበረሰቡ ጋር ያለው የግንዛቤ ሁኔታ በተሰራው ልክ ለውጥ መጥቷል፣ በሚፈለገው ልክ በህብረተሰቡ ዘንድ ጥንቃቄ እየተወሰደ ነው ለማለት አይቻልም።

የግንዛቤ ሥራዎችን ከማከናወን ባለፈ ለማንኛውም ሕንጻ ላለው ግለሰብ የሙያ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ እናደርጋለን። የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጥም ሆነ ለመኖሪያም ቢሆን ሕንጻው ማሟላት የሚገባው የደህንነት መስፈርቶች እና መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች የሙያ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ እናደርጋለን። ከዚህ አለፍ ሲልም፣ የፍተሻ ሥራ ይሰራል። የደህንነት መስፈርት ስለማሟላታቸው ምርመራ በማድረግ ግብረ መልስ ይሰጣቸዋል። ብቁ ሆነው የሚገኙ ተቋማት ሲኖሩ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ።

የምስክር ወረቀት ከሚሰጣቸው ተቋማት መካከል ሆቴሎች፣ ጋራዦች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ነዳጅ ማደያዎች፣ ፋብሪካዎች እና የተለያዩ ተቋማት ሲሆኑ ብቁ ሆነው ከተገኙ የደህንነት መስፈርትን ማሟላታቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል። የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሕንጻዎች የምስክር ወረቀት መውሰድ አይችሉም። በከተማችን የደህንነት መስፈርት የሚያሟሉ ሕንጻዎች ትንሽ በመሆናቸው ተቋማችን ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የደህንነት መስፈርት እንዲያሟሉ የሚያስችል አሠራር ዘርግታችኋል? በማያሟሉት ላይ የእርምት ርምጃ ትወስዳላችሁ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** ችግሩን ለማስተካከል የከተማ አስተዳደሩ ከሰኔ ሁለት 2014 ዓ.ም ጀምሮ ደንብ አውጥቷል። ደንቡን ማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ በተቋሙ ተዘጋጅቶ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኳል። ጸድቆና ምዝገባ አልፎ ሲመጣ ከማስተማር ባለፈ ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ ይጀመራል። ምናልባትም ይህ ተግባራዊ ሲደረግ ሁኔታው ሊቀየር ይችላል። በሌላ በኩልም ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት በጋራ በመሆን በቅርበት እየሰራን ነው።

ከዚህ በፊት ቱሪዝም ሚኒስቴር ለሆቴሎች ሰጥቶት የነበረው የኮከብ ደረጃ በመጪው መስከረም ላይ ይከልሳል። ነባሩን በመሰረዝ በአዲስ መልክ ሰርተፊኬት ይሰጣል። የእሳት አደጋ የደህንነት መስፈርትን ያላሟላ ሆቴል በሙሉ የኮከብ ደረጃ እንዳያገኝ በማድረግ ቱሪዝም ሚኒስቴር እየተባበረ ነው። ስለሆነም ይህ አፈጻጸም ይሻሻላል ተብሎ ይጠበቃል።

የት አካባቢ ምን ዓይነት አደጋ ሊከሰት ይችላል? በሚል እሳቤ የአደጋ ጥናት እንሰራን። አሁን የምንገኝበት ወቅት ክረምት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጎርፍ አደጋ ሊከሰት የሚችልባቸው ቦታዎች በእሳት አደጋ ኮሚሽን ተለይቷል፣ የመሬት መንሸራተት ሊከሰትባቸው የሚችሉ እና ሰፋ ያለ የትራፊክ አደጋም ጉዳት ይደርስባቸዋል የሚባሉ አካባቢዎች እንዲሁ ተለይተዋል።

በአጠቃላይ በአራቱ የአደጋ ዓይነቶች 505 የሚሆኑ ቦታዎች በጥናት የተለዩ ሲሆን ከነዚህ ቦታዎች ውስጥ በጎርፍ አደገኛ ናቸው ተብለው ከተለዩት 135 በቦታዎች ላይ በቶሎው የመፍትሔ ርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል። ችግሩ ከመድረሱ በፊት ቅድመ መከላከል እንዲኖር ኮሚሽኑ ለስምንት ተቋማትና ለ11ዱ ክፍለ ከተማ አስተዳደሮች በማሰራጨት መነሳት የሚገባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከቦታው እንዲያስነሱ ተደርጓል።

ለአደጋ ተጋላጭ ናቸው ተብለው ከተለዩት አካባቢዎች በአጋጣሚ የከተማ አስተዳደሩ ከተማዋን ዘመናዊ ለማድረግ በሚከናወነው የኮሪደር ልማት መቀነስ ተችሏል። ከዚህ በፊት የፍሳሽ መሠረተ ልማት አልነበረም። የኤሌክትሪክ መስመሮችም በብዙ ቦታዎች በአየር ላይ የተዘረጉና የተጠላለፉ እና አደጋን የሚያስከትሉ ነበሩ። ወንዝ አካባቢዎች በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ይኖሩ የነበር ሲሆን አሁን ላይ ችግሮቹን በኮሪደር ልማት ሥራው መቅረፍ ተችሏል።

ቀበናን ጨምሮ ከቤተ መንግሥት እስከ እንጦጦ እየተደረገ ባለው የማልማት ሥራ የአደጋ ስጋት ሁኔታው በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ ነው። በወንዙ ግራና ቀኝ ሰፍረው የነበሩ፣ ተንጠልጥለው የነበሩ ቤቶች በሙሉ ተነስተው ነዋሪዎቹ በምትኩ የተሻለ የመኖሪያ ቦታ ተሰጥቷቸው ከአደጋ ቦታ በመራቃቸው ችግሩ ተወግዷል።

መንገድ በጣም ጠባብ የነበረባቸው የመኪና አደጋ በተደጋጋሚ ይከሰትባቸው በነበሩ ቦታዎች ላይም መንገድ እየሰፋ የእግረኛ መንገድና ዋና መንገድ እየተለየ በመሄዱ አደጋ እየቀነሰ ነው። በአየር ተጠላለፍው የሚሄዱት የቴሌ፣ የመብራት መሠረተ ልማት በኮሪደር ልማቱ ከመሬት በታች እየተቀበሩ እየሄዱ በመሆኑ መሠረታዊ ለውጥ እየመጣ ነው።



**አዲስ ዘመን፡- የተቋማትና የድርጅቶች አደጋን የመቀነስ ልምድ ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሚያስተዳድሩት ሕንጻ ላይ አደጋ ይከሰታል ብለው ቀድመው የመዘጋጀት ችግሮች አሉ። ብዙ ሕንጻዎች የአደጋ መከላከያ መስፈርት የላቸውም። የደህንነት መስፈርት አያሟሉም።

አዲስ አበባ እያደገች ነው፣ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች እየተገነቡ ስለሆነ ይህን የሚመጥን የአደጋ ደህንነት መስፈርት ማሟላት እየቻሉ አይደለም። የኮንስትራክሽን ሥራ ሲሰራ ሊደረግ የሚገባቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች አሉ። የሕንጻ የአደጋ የመከላከል ሕግ አለ። በዚህ መሠረት በዲዛይን ውስጥ አካትተው የግንባታ ፈቃድ ሲወስዱ የደህንነት መስፈርት ማሟላት ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ከግንባታ ጽሕፈት ቤት ጋር በመቀናጀት ለመሥራት ሙከራ እየተደረገ ነው።

ብዙ ሕንጻዎች ኮሚሽኑ ለፍተሻ ሲሄድ ያዘጋጃሉ። ነገር ግን እውነታ ላይ የተመሠረተ ሥራ አይሰሩም። ደህንነት ለራስ ነው፣ የራሳቸው ተቋም እና ሠራተኛ ለመጠበቅ የሚሰራ በየስድስት ወሩ በባለሙያ ታይቶ የሚሞላ እሳት ማጥፊያ ሊኖራቸው ይገባል። እሳት ሲነሳ መልዕክት በቶሎ እንዲደርስ የሚያደርግ ‹ዲቴክተር› መሳሪያ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። አንድ ሕንጻ አደጋ ቢያጋጥመው እሳት አደጋ እስከሚደርስ ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲከላከል የሚያደርግ ዝግጁነት ሊኖር ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በከተማችን ምን ያህል ሕንጻዎች የደህንነት መስፈርት አሳቸው ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** ባለፉት ዓመታት በተሰራው የቁጥጥር ሥራ ከ20 ሺ በላይ ሕንጻዎችን ፈትሸናል። በዚህ ዓመት ለ200 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ43 ድርጅቶች ብቻ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል። በተቋማችን ከታዩ ከ20 ሺህ ሕንጻዎች የእሳት መከላከያ መስፈርቱን ያሟሉና እውቅና የተሰጣቸው 43ቱ ብቻ ናቸው ። ከእዚህ ውጭ ያሉ ድርጅቶች የደህንነት መስፈርቶችን ባለማሟላታቸው ሰርተፊኬት አላገኙም። አንዳንዶች መስፈርቱን ቢያሟሉም ሰርተፊኬት ያልወሰዱ አሉ። ለምሳሌ በቅርብ እየተገነቡ ካሉ ተቋማት መካከል ዓድዋ ዜሮ ዜሮ ፕሮጀክት ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ የጠበቀ ግንባታ ነው። የደህንነት መስፈርት ማሟላቱን የምስክር ወረቀት ሊወስድ ይገባል የሚል አቋም አለን። ኃይሌ ግራንድ ሆቴል ደረጃው የጠበቀ ነው። ነገር ግን እስካሁን የደህንነት ስርተፊኬት አልወሰደም። መስፈርቱን አለማሟላት የሚስተዋልባቸው እንደ ማደያዎች፣ ፋብሪካዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ ሞሎች፣ መኖሪያ ሕንጻዎች፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ናቸው።

በበጀት ዓመቱ በዘጠኝ ወር ውስጥ በተደረገው ግምገማ ከስድስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር በላይ ንብረት በአደጋ ወድሟል። ይህ ሀብት ለዚች ሀገር ትልቅ ሀብት ነው። ባለን ውስን ሀብት ከአደጋ ራሳችን ካልጠበቅን የውድመት መጠኑ በጣም ከፍተኛ ነው። ከዚህ በላይ በገንዘብ የማይተመን የሰው ሕይወት ይጠፋል። በኮንስትራክሽን ሂደት ላይ ከሕንጻ ላይ ወድቀው ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎች አሉ። መርካቶ አካባቢ በመደርመስ አደጋ ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎች አሉ፡ በማሽነሪ ሊቆፈር የሚገባው በሰው በማስቆፈር ተንዶ ሕይወታቸውን ያጡ አሉ። በጎርፍ ጭምር በዚህ ዓመት ሰባት የሚሆኑ ሰዎች ተወስደዋል። በተለያየ መንገድ ሕይወታቸው እያጡ ያሉት ወጣቶች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በገንዘብ የሚተመን ንብረት ወድሟል፣ የሰው ሕይወትም ጠፍቷል። ነገር ግን ከውድመትና ከጥፋት የታደጋችሁት ሀብት እና የሰው ሕይወት የለም?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** የምናድነው የሰው ሕይወትና ንብረት ከሚጠፋው በብዙ እጥፍ ይበልጣል። በዘጠኝ ወር ብቻ ሰባት ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ከውድመት መታደግ ተችሏል። ከሚጠፋው የሚድነው ይበልጣል። የተቋሙ ሠራተኞች ብዙ ያልተመቻቹ ነገሮች እያሉ ንብረትና ሕይወትን አድነዋል።

የከተማችን የትራፊክ ፍሰት ሁኔታ አሁን የሚሰራው መንገድ ያለው ነገር ተስፋ ሰጭ ሁኔታ ቢኖርም በጣም አስቸጋሪ ነው። እሳት አደጋ ተከስቶ በቦታው ለመድረስ መንገድ ይዘጋል። አደጋው በተከሰተበት ቦታ ከደረስን በኋላም ኤሌክትሪክ ካልተቋረጠ ርምጃ መውሰድ አይቻልም። ውሃ ሲረጭ ኤሌክትሪክ ካለ አደጋ ሠራተኞቹ ጉዳት ውስጥ ይወድቃሉ።

የከተማው እድገት እና ከሕዝብ ብዛት ከተቋሙ አቅም አንጻር ሥራችንን ፈታኝ እያደረገው ነው። በከተማዋ የሚስተዋለው የትራፊክ መጨናነቅም በሥራችን ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እያሳደረበን ነው። በሀገራችን ለእሳት አደጋ መከላከያ የተሽከርካሪዎች ብቻ ጥቅም የሚሰጥ መስመር ስለሌለ የሚፈጠረውን አደጋ በአጭር ሰዓት ደርሶ ለመከላከል አያስችልም። በሌሎች ሀገራት የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ የሚጓዘው በራሱ መስመር ነው። በመሆኑም በሚፈለገው ፍጥነት አደጋው በተፈጠረበት ቦታ ደርሶ መከላከል ያስችለዋል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ተጠየቅ

# “ከ20 ሺህ ሕንጻዎች የእሳት መከላከያ ...

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

በሌሎች ሀገራት የእሳት አደጋን ለመከላከል ድሮኖችን ይጠቀማሉ። ድሮኖች ካሉ አደጋ በደረሰበት ቦታ በሰከንዶች ውስጥ በመድረስ እሳቱ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ በቁጥጥር ስር ማዋል ይቻላል። እኛም ከድሮን ጋር ተያይዞ ለከተማ አስተዳደሩን ጥያቄ አቅርበናል።

ከድሮን በተጨማሪ ተቋማችን ለማዘመን እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥራ ለመሥራት የተለያዩ ርምጃዎችን ጀምረናል። ከእነዚህ ሥራዎች መካከል አደጋዎች በደረሱ ወቅት ጥሪዎች በተገቢው መንገድ እኛ ጋር እንዲደርስ ማድረግ የሚያስችል ነው። ይህን ቴክኖሎጂ ከመጠቀማችን በፊት ደዋዮች ራሱ በቀጥታ ሊያገኙን የሚችሉበት እድል ጠባብ ነበር።

ሌላው ተቋማችን የተጠቀመው ቴክኖሎጂ ደግሞ ሀሰተኛ ጥሪዎችን መለየት የሚያስችል ነው። ይህን ቴክኖሎጂ መተግበር ከመጀመራችን በፊት በአንድ ቀን ውስጥ እስከ ሶስት ሺህ የሚደርሱ ሀሰተኛ ጥሪዎች እናስተናግድ ነበር። ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በሰራነው ሥራ ሀሰተኛ ጥሪዎችን መለየት የምንችልበት በመፈጠሩ ሀሰተኛ ጥሪዎችን መቀነስ ተችሏል።

ሌላው ተቋማችን በዘንድሮው ዓመት ለመተግበር ከጫፍ ላይ የደረሰው ቴክኖሎጂ ተሽከርካሪዎች ላይ በሚገጠም ካሜራ አማካኝነት የአደጋ ቦታዎችን እና አጠቃላይ ሁኔታዎችን ቢሮ ላይ ሆነን መከታታል የሚያስችል ነው። ለምሳሌ የመንገድ አማራጭ፣ አደጋው የት ጋር ነው? አደጋው ስፋቱ ምን ያህል ነው? ስንት መኪና ያስፈልገዋል? በየት በኩል መኪና መላክ እንችላለን? ትራፊክ መጨናነቅ የሌለው በየት በኩል ነው? የሚለውን እና መሰል ጥያቄዎችን መፍታት የሚያስችል ነው። አሁን ላይ ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ የምናደርግበት ሥርዓት እየዘረጋን ስለሆነ የምናሻሽለው ነገር ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ቴክኖሎጂው መቼ ተጠናቆ ወደ ሥራ ይገባል?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** ሁለተኛው የቴክኖሎጂው ፌዝ በዚህ በጀት ዓመት ሁለት ወራቶች ውስጥ ተጠናቆ በመስከረም ወር አካባቢ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። መኪና ላይ የምንገጥመውን ካሜራ በተመለከተ በኢኖቬሽን ቢሮ አማካኝነት በውጭ ድርጅት እየተሰራ ነው። ሂሊኮፍተር እና ድሮን የምንታጠቅበትን ጊዜ መቁረጥ አንችልም። ነገር ግን ሂሊኮፍተር እና ድሮን ለመግዛት ከተማ አስተዳደሩ ቃል ገብቶልናል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ቢሮ ከስትራቴጂክ እቅድ አንጻር ሂሊኮፍተር እና ድሮን መቼ ለመግዛት እቅድ ይዛችኋል?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** እኛ የአምስት ዓመት የሪፎርም እቅድ አለን። በሪፎርም እቅዳችን ውስጥ ሂሊኮፍተር እና ድሮን በተመለከተ ታሳቢ አድርገናል። ይህን መሠረት አድርገን ባለፈው ዓመት ጀምሮ ለከተማ አስተዳደሩ ጥያቄ አቅርበናል። ክብርት ከንቲባዋም ቃል ገብተዋል። አሁን ላይ ያለው የኮሪደር ልማት ከፍተኛ የበጀት አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ የመጀመሪያው ትኩረት እዚያ ላይ ነው። በዚህ አምስት ዓመት ውስጥ ግን ይሟላል ብለን እናስባለን። እሱን ስናገኝ አስተማማኝ የሆነ የመከላከል ሥራ እንሰራለን። ነገር ግን ምንም ነገር ቢኖር ደግሞ ከአደጋ በፊት የሚሰራውን ሥራ አይተካም። ሰው አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ነገሮች ላይ እስካልተጠነቀቀ ድረስ ሁሌም እየሄድን እሳት ማጥፋት ነው የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- አብዛኛው የአደጋ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** ባለፈው ዓመት ፖሊስም ባደረገው የምርመራ ሥራ ከ10 እስከ 15 በመቶ የሚሆኑት አደጋዎች የወንጀል ምልክት ያላቸው ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ ሰዎች ኢንሹራንስ ለማግኘት ተብለው እሳት የሚያስነሳባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። 80 እና 90 በመቶ የሚሆነው ግን ከጥንቃቄ ጉድለት የሚያመጣቸው አደጋዎች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- አደጋን ለመቀነስ ጥናቶች እንደሚደረጉ ይነገራል። ካለፉት ዓመታት አንጻር ያለው ሁኔታ ሲታይ አሁን ላይ አደጋዎች ጨመሩ ወይስ ቀነሱ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** አደጋ የመቀነስ ሁኔታው ብዙ አይደለም። ይህ ማለት ግን የአደጋ ቅነሳ ሥራ ስላልተሰራ ነው ማለት አይደለም። የሀገር እድገት፣ የሕዝብ ብዛት፣ የአየር ንብረት ለውጡ የሚፈጥራቸው ሁኔታዎች አሉ። የባለፈው ዓመት የአየር ሁኔታና የዘንድሮው ዓመት የአየር ሁኔታ ከአስር ዓመት በፊት ከነበረው የአየር ሁኔታ የተለየ ነው። አሁን ላይ ያለው የሰዎች የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁ የተለየ ነው። ከገጠር ወደ ከተማ የሚመጣው ሕዝብ ብዛት እየጨመረ ነው። ይህ ሕዝብ ደግሞ የሚሰፍርበት ቦታ ይፈልጋል። በሕጋዊም ሆነ ሕገ ወጥ መንገድ ወንዝ እና ገደላማ ቦታዎች አካባቢ ጭምር ይሰፍራል። ይህ ደግሞ ለአደጋ ይጋለጣል። በእነዚህ እና መሰል ምክንያቶች በከተማችን አደጋ የመቀነስ ነገር አይታይበትም። ነገር ግን አደጋን የመቀነስ ሥራ ባንሰራ ኖሮ ሊደርስ ይችላል ብለን የምንገምተው እና የሚደርሰው በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ አለው። ስለሆነም የመከላከል ሥራችን ውጤታማ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሌሎች ሀገራት የአደጋ ተሽከርካሪዎች የራሳቸው የሆነ መስመር አላቸው። አሁን እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማት የአደጋ ተሽከርካሪዎች የራሳቸው የሆነ መስመር እንዲኖራቸው ለማስቻል ከከተማ አስተዳደሩ እና ከመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር ተናባችሁ ከመሥራት አንጻር ያለው ነገር ምን ይመስላል?**

**አቶ ይከፈለው፡-** የዘለቄታ መፍትሔ የሚሆነው አስቻይ አሠራሮችን መዘርጋት ነው። በሪፎርማችን ውስጥ ብዙ ጉዳዮች አንስተናል። ከዚህ ውስጥ በትራፊክ ማኔጅመንት ለማስተናገድ እድል እንዲያገኙ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች እንደ ፖሊስ እና መከላከያ የተለየ ታርጋ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየሰራን ነው። ለምሳሌ አምቡላንስ የሚጠቀሙ ተቋማት የራሳቸው የሆነ መለያ ድምጽ ይኖራቸዋል። በተመሳሳይ ለእኛ ተሽከርካሪዎችም የራሱ መለያ ድምጽ ሊኖረው ይገባል። ነገር ግን አሁን ላይ ለእሳት አደጋ ተብሎ የተለየ መንገድ የለም። በሂደት ግን ታሳቢ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ 20 ሺህ ሕንጻዎች የእሳት መከላከያ መስፈርቱን እንዲያሟሉ መዝግባችሁ ነበር። ነገር ግን መስፈርቱን ያሟሉ እና እውቅና የተሰጣቸው ለ43 ብቻ ነው። መስፈርቱን ባላሟሉ እና እውቅና ባልያዙ ሕንጻች ላይ ምን ርምጃዎችን ወሰዳችሁ? ያንን ማስፈጸም የሚያችል የሕግ ማዕቀፍ አላችሁ?**

**አቶ ይከፈለው፡-** የሕንጻዎችን የእሳት የመቆጣጠር አቅም የምንለካባት ሕግ አለን። ይህም ሰኔ 2014 ዓ.ም የከተማ አስተዳደሩ ያወጣው ነው። ሕጉ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ የሆኑ ተቋማትን ያስገድዳል። የአደጋ ደህንነት መስፈርት ያላሟላ ተቋም ከገንዘብ ቅጣት ጀምሮ ተቋሙ አገልግሎት እንዳይሰጥ እስከ ማድረግ ድረስ ርምጃ ይወስዳል።

ነገር ግን ሕጉ ማስፈጸሚያ መመሪያ አልነበረውም። አሁን ላይ ለሕጉ ማስፈጸሚያ የሚሆነው መመሪያ እንዲጸድቅ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኳል። መመሪያው ተመዝግቦ እና ተቀባይነት አግኝቶ ሲመጣ ተግባራዊ ማድረግ እንጀምራለን። ከችግር መውጫ መንገድ ይሆናልም ብለን እንጠብቃለን። ሕጉን መስከረም ላይ ወደ ትግበራ እናስገባለን ብለን እንጠብቃለን።

መመሪያው ባይወጣም ሕጉን ተንተርሰን የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን ስንሰራ ቆይተናል። ሰኔ 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸደቀው ሕግ የደህንነት መስፈርት በማያሟሉ ሕንጻዎች እና ሆቴሎች ላይ መጀመሪያ እስከ መቶ ሺህ ብር ድረስ እንደሚቀጣ እና ከስህተቱ የማይመለስ ከሆነ ደግሞ የንግድ ፍቃዱ ይሰረዝና በመጨረሻም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እስከ መዘጋት እንደሚደርስ ይደነግጋል።

ይሄንን ሕግ ለፋብሪካዎች፣ ለሆቴሎች እና ለነዳጅ ማደያዎች ሰብስበን ላለፉት ሁለት ዓመታት እያስተማርን ቆይተናል። መስከረም ላይ ወደ ትግበራ እንገባለን። በሕንጻ ፈቃዱ በኩል ዲዛይኑ ውስጥ ማካተት አለበት። ሕንጻ ሳይጠናቀቅ ወደ ትግበራ በማስገባት ከሕንጻ ቁጥጥር እና ፈቃድ ባለስልጣን ጋር ሕጋችንን ለማጣጣምና በጋራ ለመሥራት እየተንቀሳቀስን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከአዲስ አበባ ውጭ በሆኑ ከተሞች ላይ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ አኳያ ያሏችሁ ሚና ምን ይመስላል?**

**አቶ ይከፈለው፡-** የእኛ ተልዕኮ አዲስ አበባና ዙሪያዋ ባሉ ከተሞች የሚፈጠሩ አደጋዎችን መከላከል ነው። ከአደጋ ደህንነት አንጻር እስከ ዞን ድረስ ሰፋ ያደርገዋል። ከዚያ ውጭ ግን በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብልን ከአዲስ አበባ ውጭም የምንሰራበት



አግባብ አለ። ለምሳሌ ቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር አብረን ስለምንሰራ ከአዲስ አበባ ውጭ ለሚገኙ ሆቴሎች እውቅና ስልጠና የሰጠናቸው ሆቴሎች አሉ።

የሰብዓዊ ጥያቄ ስለሆነ የትም ቦታ ቢሆን እኛ ስንጠየቅ አገልግሎቱን እንሰጣለን። በዚህ ዓመት አደጋ ያጋጠማቸው ክልሎች ላይ በዋናተኞቻችን አስከሬን ያወጣበት ሁኔታ አለ። ኦሮሚያ ላይ በየቀኑ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ አደጋ ሲከሰት በቦታው ተገኝተን እንከላከላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ እና አደጋን ለመከላከል ቁርጠኛ አመራር እንዲኖር ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር በምን መልኩ ተናባችሁ እየሰራችሁ ትገኛላችሁ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** እስካሁን ቁርጥ ያለ ርምጃ መውሰድ ያልቻልነው የሕግ ማዕቀፉ ክፍተት ስለነበረ ነው። በሕንጻ ሕጉ ጅምር ሕንጻዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ይፈቅዳል። የእኛ ተቋም ደግሞ በጅምር ሕንጻዎች ችግር ሊፈጠር ስለሚችል አገልግሎት እንዳይሰጡ አቋም አለን። ይህ የአሠራር ልዩነት ለአደጋዎች መፈጠር በር እየከፈተ ይገኛል።

በግንባታ ወቅት ለሚደረግ ጥንቃቄ ላይ ሕጉ ክፍተት የለበትም። ርምጃ መውሰድ ያለበት ተቋም ርምጃ ያለመውሰድ ክፍተት ነው። ይህንን ተጠያቂ የማድረግ ያስፈልጋል። ርምጃ በማይወስዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ተጠያቂ የሚደረግበት አግባብ በእኛ ተቋም ሕግ ወጥቶለታል። ማስፈጸሚያ መመሪያው በእጃችን ሲገባ፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አንድ ሕንጻ በግንባታ ላይ እያለ ተገቢውን ቁጥጥር ሳያደርጉ ቀርተው አደጋ ቢያጋጥም እና የሰው ሕይወት ቢያልፍ የመጀመሪያ ተጠያቂ የምናደርገው የመንግሥት ተቋም የሆነውን የግንባታ ፈቃድ እና ተቆጣጣሪውን ነው።

ክትትል ሲያደርጉ ደህንነቱ ባልተጠበቀ መወጣጫ ላይ ሲያሰራ የሚገኝ ሕንጻ ላይ ያለ ምህረት ርምጃ መውሰድ አለባቸው። ይህንን ካላደረጉ እነሱ ተጠያቂ ይሆናሉ። በማሽነሪ የሚቆፈረውን ጉድጓድ በሰው ጉልበት የሚስቆፍር ኮንትራክተር ሲያገኙ ርምጃ መውሰድ አለባቸው። ይህንን ካላደረጉ እኛ የምንጠይቀው እነሱን ነው።

ሕጉ ወደ ሥራ ሲገባ ቆራጥ ርምጃ ለመውሰድ ያስችለናል። እኛ እስከ ዛሬ ከማስተማር እና ከመምከር ባለፈ ሕግ ለማስከበር የሚስችል ስልጣን አልነበረንም። ሕጉ የወጣው ሰኔ 2014 ነው። ሕጉን በደንብ አስተምሮ በመመሪያ ተደግፎ ወደ ሥራ መግባት ውጤታማ ያደርጋል። የአደጋን ጉዳይ ከኛ በላይ የሚገነዘብ የለም፤ እኛ በተግባር አይተናል። ስለሆነም ሕግ በማያከብሩ እና በማያስከብሩ አካላት ላይ እኛ ጠብቀን ርምጃ መውሰድ አለብን ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- የተቋማችሁ ሠራተኞች በሥራ ላይ እያሉ አደጋዎች ቢደርስባቸው ካሳ ከመክፈልስ አኳያ አሰራራችሁ ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** በእኛ ተቋም የሚሠሩ ሠራተኞች እንደ ማንኛውም ሲቪል ሰርቫንት መታየት የለባቸውም። ምክንያቱም ሕይወታቸውን ሰጥተው በመስጠት ሕይወት ያድናሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከተማ አስተዳደሩ እያየው ያለው ነገር አለ። በሥራ ላይ እያሉ ጉዳት ቢደርስባቸው እና በጉዳት ምክንያት ከሥራ ቢወጡ መቋቋም የሚያስችል የተሻለ የደሞዝ እና የተለያዩ የጥቅማ ጥቅም የክፍያ ሥርዓት ሊኖራቸው ይገባል።

አሁን ላይ የአካል ብቃት የሚሰሩበት የስፖርት ጅምናዚየም፣ የተሻለ ካፍቴሪያ፣ ተገቢው ደምዝ እና ጥቅማ ጥቅም፣ ተገቢ የአደጋ ጊዜ አልባሳት እንዲኖራቸው ለማድረግ የጀመርናቸው ሥራዎች አሉ። ከተማ አስተዳደሩም እያገዘን ነው። በዚያ መንገድ ሪፎርም ሠራውን ለማሳካት እየሰራን ነው።

በርግጥ ሠራተኞቻችን የመድህን ዋስትና አላቸው። ነገር ግን አካል ቢጎድላቸው ፤ ሕይወታችውን ቢያጡ የካሳ ክፍያው ምን መሆን አለበት የሚለውን ግን አሁንም ገና ብዙ ማሰብ ይጠይቃል። ከኢንሹራንስ ካምፓኒዎችም ጋር የተለየ ስምምነት ይጠይቃል። ደሞዛቸውን እና ጥቅማ ጥቅማቸውን ከማሻሻል ባለፈ የመድህን ዋስትናቸውን ማሰብ ይጠይቃል።

ከዚህ በፊት ተቋሙ የሚመራው በሲቪል ሰርቪስ ሕግ ነበር። አሁን ራሱን የቻለ “የፓራ ሚሊታሪ” ደንብ ወጥቶለት እድገታቸውንም ሆነ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ታሳቢ ያደረገ ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው። በቂ አይደለም በሌላው ዓለም አደጋን የሚከላከሉ ሰዎች በማህበራዊ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል። የአደጋ ሠራተኛ ነው ከተባለ ባቡር ላይ ተነስቶ ጭምር ሰው ያስቀምጠዋል። ያለ ወረፋ እና ሰልፍ አውሮፕላን እንዲሳፈር ይደረጋል። ይህን ክብር ወደሀገራችን ለማምጣት እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለቀይ መስቀል ወይም ተመሳሳይ ተቋማት ከመንግሥት ሠራተኞች እና ዜጎች የሚቆረጥ ገንዘብ አለ። ከዚህ አግባብ የድርጅቱን ገቢ ለማሳደግ ምን እየሰራችሁ ነው ?**

ኮሚሽነር ይከፈለው፡- ይህን ለማድረግ ሃሳቡ ስላለ በሪፎርም እቅዳችን ውስጥም አለ። ለዚህ ደግሞ ሕግ ማዘጋጀት ይኖርብናል። ይህ ዓይነት አሠራር ሌላው ዓለም ላይ አለ። አሁን ላይ ድጋፍ እንኳን የጠየቅናቸው ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና ባንኮች ብዙም የሚያጠግብ ምላሽ አልሰጡንም። መሆን የነበረበት ግን በቋሚነት ለእሳት አደጋ ካሚሽኑ መቁረጥ ነበረባቸው ይህን ለማድረግ ሕግ ያስፈልጋል ብለን ሥራ እየጀመርን ነው። በቀጣይ ዓመት በርግጠኝነት እሱን እናጸድቃለን ብለን እናስባለን። በሕግ የሚመራ ድጋፍ እና ገቢ ይኖረናል። ያ ሲሆን ልዩ ክፍያ እና ልዩ ጥቅማ ጥቅም ማሟላት ያስችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- በሰው ኃይል እና በመሳሪያ ከተማዋን የሚመጥን የተደራጀ ሥራዎችን ለማከናወን የያዛችሁት እቅድ ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** እቅድ አለን። በአምስት ዓመት ውስጥ ምን ያህል ተጨማሪ የአደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ እና አምቡላንስ ለመጨመር፤ አንድ ሄሊኮፕተር እና አንድ ድሮን ለመግዛት በስትራቴጂክ እቅዳችን ላይ ይዘናል። ይህም ከከተማው ገቢ ጋር እየተጣጣመ እና እየታየ የሚሰራ ይሆናል። ቅርንጫፍ በመስፋትም ረገድ አሁን ላይ 26 ቅርንጫፎች ያስፈልጉናል። ባለፈው ዓመት ሪፎርሙን ስንጀምር ዘጠኝ ቅርንጫፎች የነበሩ ሲሆን አሁን 11 ደርሰናል። በሚቀጥሉት ዓመታት ነገሮችን እያየን ቅርንጫፎችን የምንከፍት ሆኗል።

አንድ ቅርንጫፍ ሲጨመር ታሳቢ የሚደረጉ በርካታ ነገሮች አሉ። የሰው ኃይል፣ ተሽከርካሪ፣ የሥራ ቦታ እና ሌሎች ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነዚህን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት አቅማችንን እያየን ስታንዳርድ ማሟላት አለብን። አደጋ መከላከል ጋር ተያይዞ ዓለም ላይ ስታንዳርድ አለው። ለምን ያህል ሕዝብ እና ለምን ያህል የቆዳ ስፋት ስንት “ፋየር ፋይተር”? ፣ ስንት የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ? ስንት አምቡላስ መኖር እንዳለበት ዓለም አቀፍ ስታንደርድ አለ። እኛም በኮተቤ ዩኒቨርሲቲ አስጠንተን ስታንዳርዱን ለማሟላት እቅድ ይዘን እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማሰልጠኛዎቻችሁን በማዘመን፤ የውጭውን ዓለም ተሞክሮ ለሰልጣኞቻችሁ ከመስጠት አንጻር ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** የውጭው ዓለም የደረሰበትን የአደጋ መከላከል ሥርዓት በሀገራችን እንዲኖር እና ሰልጣኞቻችንም የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸው ለማስቻል የውጭ ሰዎች እዚህ ድረስ መጥተው ስልጠና እየሰጡ ነው። እድሉ ሲገኝም ሠራተኞቻችንን ወደ ውጭ ሀገር ልከን እናስተምራለን። በርግጥ አሁን አሁን እንደዚህ ዓይነቱ አሠራር እየቀነሰ ነው። በቀደመው ጊዜ የእሳት አደጋ ተከላካይ ሰልጣኞች በብዛት ወደ ውጭ ሄደው እውቀት የሚያገኙበት አግባብ ነበር። አሁን ላይ አንድ አመራር እና 10 ባለሙያዎች ለስልጠና ኮሪያ ሀገር ናቸው። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም። ተጨማሪ ሥራን ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**ኮሚሽነር ይከፈለው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ምርታማነትን ማሳደግ ከኑሮ ውድነት ለዘለቄታው መውጫ መንገዳችን ነው

**ታሪኩ ዘለቀ**

የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ የዓለም ገንዘብ ድርጅት አሊያም የተለያዩ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበራት በየጊዜው የየሀገራትን የገንዘብ የመግዛት አቅምን፣ የኑሮ ውድነትን ወይም ግሽበትን በተመለከተ መረጃዎችን ያወጣሉ።

በሚወጡት መረጃዎች በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ የምጣኔ ሀብቱ የደረሰበት ደረጃ ከዜጎች የገቢ ብሎም ኑሮ መመጣጠን አንፃር የልኬቱ አንዱ መስፈርት ሆኖ ይቀርባል። በተለይ ደግሞ ምጣኔ ሀብቱን ስናነሳ ዜጎች በሂደቱ ውስጥ ያላቸው ተጠቃሚነት ከገቢና ኑሮ ተመጣጣኝነት በኩል መመልከታችን የሚጠበቅ ነው።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ተመጣጣኝ የዋጋ ንረት አስፈላጊ ነው። ምን ያክል ነው የሚለው በጥናት የሚመለስ ቢሆንም ከተወሰነ በላይ ሲሆን ማህበረሰብን ይጎዳል። ሁሉ ነገር በሚወደድበት ጊዜ ኑሮ ይከብዳል። በውድነቱ ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት ለኑሮ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ተለይተው ነው።

ከእነዚህ ውስጥ ምግብ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። የምግብ ሸቀጦች በሚወደዱበት ጊዜ ኑሮ በአጠቃላይ እንደተወደደ ተደርጎም ይወሰዳል። እውነታውም ይኸው ነው። ርግጥ ነው የኑሮ መወደድ የዓለም ሀገራት ችግር ከሆነ ሰነባብቷል። በመላው ዓለም ላይ የተከሰተ ጉዳይ መሆኑን የዓለም ባንክም ሆነ የዓለም ገንዘብ ድርጅት በየጊዜው የሚያወጧቸው ሪፖርቶች እያመላከቱ ነው።

ነገር ግን በአደጉት ሀገራት የኑሮ ውድነቱን ለመቋቋም የሚያስችል የዳበረ አቅም አላቸው። የፈለገ ነገር ኑሮ እየጨመረ ቢውል ኑሯቸው ላይ የሚያስከትለው ነገር የለም። የኑሮ ውድነት አቅመ ደካሞች በሆነው ወይም ባላደግነው እንደ እኛ ባሉ ሀገራት ግን ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል።

ለምሳሌ ሰሞኑን ሲኤንኤን ባቀረበው የውይይት መድረክ በአሜሪካ ኑሮ እጅግ እንደተወደደ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እየተወያዩበት ነበር። አምና ይገዟቸው የነበሩ አንዳንድ እቃዎች፣ ምግቦችና ሌሎች አገልግሎቶች ላይ እያንዳንዱ አሜሪካዊ የ925 ዶላር ጭማሪ ወይም ግሽበት /ኢንፍሌሽን እንደተጨመረባቸው በውይይታቸው ተጠቅሷል።

ለመጨመሩ ኮቪድ19፣ የዩክሬን ጦርነት፣ የጋዛን ጦርነትና ሌሎች ጉዳዮችን እንደ ምክንያት አቅርበዋል። የኢኮኖሚ ባለሙያዎቹ የጠቀሷቸው ምክንያቶች እኛም ሀገር ላይ ችግር ፈጥረዋል። ነገር ግን ከቁጥጥር ውጭ የሚሆኑ ነጋዴዎች የሚጨምሩት ሰው ሠራሽ / አርቴፊሻል ጭማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በመኖሩ ችግሩን ይበልጥ ያባብሰዋል።

በኢትዮጵያ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት መባባስ መንስኤ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉት በተደጋጋሚ ተነግሯል። ቅጥ ያጣው የግብይት ሥርዓት፣ ፈርጣማው የደላሎች እጅ ገበያን ለማረጋጋት ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት በሚገባቸው ልክ የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋት፣ የማይገባ ትርፍን የሚፈልጉ ነጋዴዎች መበራከት ከብዙ በጥቂቱ ናቸው።

ቅጥ ያጣው የግብይት ሥርዓት፣ ፈርጣማው የደላሎች እጅ ገበያን ለማረጋጋት ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት በሚገባቸው ልክ የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋት፣ የማይገባ ትርፍን የሚፈልጉ ነጋዴዎች መበራከት ከብዙ በጥቂቱ ናቸው

እነዚህን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ በዋጋ ንረቱ ዙሪያ እየተወሰዱ ያሉ ማስተካከያ ርምጃዎች በሀገሪቱ የሚታየውን የኑሮ ውድነት ወይም ጤናማ ያልሆነውን ንረት ማስተካከል እንደሚያስችሉ ተስፋ ተጥሎባቸዋል። በተለይ የህብረተሰቡ መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ ምርቶች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት በተለያዩ አማራጮችና ምርታማነትን በማሳደግ ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት እንደ ቀጠለ ቢሆንም አሁንም ግን የኑሮ ውድነቱ ብዙ የህብረተሰብ ክፍሎችን እየፈተነ ይገኛል።

ይህን የተረዳው መንግሥት ሀገራዊ የሆነውን የዋጋ ግሽበት ለመቆጣጠር እና በምግብ ሰብሎች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለመከላከል በርካታ የመፍትሔ አማራጮችን ተግብሯል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ጤፍን ጨምሮ በሌሎችም የግብርና ምርቶች ላይ ከዚህ ቀደም የነበረን እሴት ታክስ ማንሳት ሲሆን ውሳኔው ገበያው ላይ መረጋጋትን በማምጣት ምርቶች በብዛት የሚገኙበትን አማራጭ ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል።

ታዲያ ትግበራው መሬት ወርዶ ሥራው መሰራት ከተጀመረ ከአንድ ወር በላይ አልፎታል። በሂደቱ ግን እስካሁን ገበያው ላይ መረጋጋት አልተመለከትንም። ምግብ ነክ የሆኑ ግብዓቶች አሁንም ዋጋቸው እላይ እንደተሰቀለ ነው። እንዳውም አንዳንዶች የምግብ እህሎች ዋጋ ከእለት ወደ እለት እየጨመረ መጥቷል።

የዚህ ምክንያት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እለት ከእለት ከሚጠቀማቸው የምግብ አቅርቦቶች ውስጥ የሚጠቀሱት ጤፍ፣ ስንዴ፣በቆሎ፣ ማሽላና ሌሎች ሰብሎች በሚፈለገው መጠን ገበያ ላይ አለመገኘታቸው ነው። የምርት አቅርቦታችን ያለበት ደረጃ ከፍላጎት ጋር ያለመመጣጠን የዋጋ ንረቱን አምጥቶታል።

የተሻለ ብር ያለው ብቻ ከፍሎ እንዲጠቀማቸው አድርጓል። በገበያው ውስጥ የሚፈለጉ ምርቶች በሚፈለገው መጠን ካልተመረተ አሊያም ገበያ ላይ ካልቀረበ የዋጋ ጭማሪን ማስከተሉ አይቀሬ ነው። ሁኔታዎች ባልተመቻቹበት ሁኔታ የዋጋ ቅናሽን ማሰብ አይታሰብም። ታክሱ ሲነሳ ዋጋቸው ይቀንሳል ቢባልም የሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ግን እሱን እያሳየ አይደለም።

ለምን አልሆነም ካልን ደግሞ የተመረቱት ምርቶች ያለ ተጨማሪ ወጪ፣ ያለ መጉላላት ወደ ገበያ የሚደርሱበት ሁኔታ በየጊዜው ከበድ እያለ መምጣቱ ነው። በተጨማሪም ተጨማሪ እሴት ታክሱ እንደተነሳ ዋጋቸው በአጭር ጊዜ ይቀንሳል ተብሎ አይታሰብም። በርግጥ የእህልና ጥራጥሬ የግብርና ምርቶችና የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦችና መጠጦች በአዲሱ መወሰኛ መሠረት ነፃ መደረጋቸው በመሠረታዊነት ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ይበልጥ ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል።

ሆኖም ግን የታሰበው ሳይሆን ነገሮች ባሉበት መቀጠላቸው የተወሰዱት ማሻሻያዎች ተፈፃሚነት ላይ ዜጎች ጥያቄ ማንሳታቸው የሚጠበቅ ነው። ማሻሻያዎቹ የታለመላቸውን ግብ አለመምታታቸው ከአቅራቢው እስከ ተቆጣጣሪዎቹ ያለውን አሰራር መፈተሽ እንደሚገባ የሚያመላክት ጉዳይ ነው። የሕግ የበላይነት በማስከበርና ተጠያቂነት በማስፈን ረገድ የተሰሩ ሥራዎች እዚህ ግባ የሚባሉ እንዳልሆኑ የሚጠቁም ነው።

የቁጥጥር ሥራ የሚሰራው አካል የማስፈፀም አቅሙ ደካማ መሆኑንም ያሳያል። ማስፈፀም የሚችል ተቋም በደከመ መጠን የሚወጡ የመንግስሥ ስትራቴጂዎች ለማህበረሰቡ እንደማይጠቅሙም ማሳያ ይሆናል። ይህም በመሆኑ የዋጋ ግሽበቱ ማህበረሰቡ ላይ ጫናው እንደበረታ ቀጥሏል። ዜጎች መግዛት እየፈለጉ እንዳይገዙ ገበያው ጫና ፈጥሮባቸዋል።

ብዙሃኑ የመግዛት አቅሙ እየተዳከመ ስለሄደ የሚጠቀማቸውንና የሚገዛቸውን መጠን በመቀነስ እየተጠቀመ ይገኛል። ይህ ማለት ታክሱ ቢነሳም አቅርቦት አብሮት በመቀነሱ የኑሮ ጫናውን ሊያግዝ አልቻለም። አሁንም ዜጎች በዋጋ ግሽበቱ የተነሳ ኑሯቸው ላይ ጫና መፈጠሩ በግልፅ እየታየ ነው።

ችግሩን ለመፍታት መንግሥት አቅርቦት ላይ የበለጠ መሥራት ይጠበቅበታል። ቁጥጥሩንም ከቀደመው በተሻለ መሥራት የቤት ሥራው ሊያደርግ ይገባል። የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት ከተቻለ ከቀረጥ ነፃ አካሄድ በአግባቡ ተተግብሮ ዜጎች ከኑሮ ጫናው ይላቀቃሉ።

ግብይቱ ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲሳለጥ ማድረግም ያስፈልጋል። ቅጥ ያጣውንና እየተባባሰ የመጣውን የግብይት ሥርዓት በሕጋዊና በአስተዳደራዊ መንገዶች ማስተካከል ይገባል። በርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ከግማሽ በላይ ያለው የዋጋ ግሽበት ሰው ሠራሽ አሊያም ሴራን መሠረት ያደረገ ነው። ጎረቤታችን ኬንያ ወይም ሱዳን አሊያም ጅቡቲ የሚገዛ አንድ ልብስ ኢትዮጵያ ሲመጣ ሶስትና አራት እጥፍ የሚጨምርበት ምንም ምክንያት ሊኖረው አይችልም።

ለዋጋ ንረቱ አሁንም ሰው ሠራሽ ምክንያት የሚታከልበት ከሆነ የገበያ ሰንሰለቱ በዜጎች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ የገዘፈ ይሆናል። ስለዚህ መንግሥት የራሱን ሥርዓት/ሲስተም ከባለሀብቱ ሥርዓት ነጥሎ ማየት አለበት። ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ቢዝነስ ላይ የተሰማሩ አካላት ላይ ርምጃ መውሰድ ይገባዋል። ገበያው ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ የሚስችል አሠራርን መዘርጋትና ገበያውን ሊያውኩ የሚችሉ ማንኛውንም ክስተቶች መቆጣጠር ያስፈልጋል።

በርግጥ ይህ ችግር በአደጉ ሀገራት ላይ ሙያዊ በሆነ መንገድ የሚወዳደሩ ቢዝነሶች/ድርጅቶች ወደ ሀገር ሲገቡ የሚፈታ ቢሆንም ዓለም አቀፍ አሠራር በመዘርጋት ዘልማዳዊ መንገድን መተው ግድ ይላል። ሙያዊ በሆነ መንገድ የማይሰራ ቢዝነስ /ግብይት ባለበት ሀገር ውስጥ ዜጎችን የሚጎዳ ሰው ሠራሽ ግሽበት መከሰቱ የማይቀር ነውና።

በአምራችና ሸማች መካከል ያለውን የፍላጎት እርቀት ማጥበብ አስፈላጊ ነው። በብዛት ከማምረት ይልቅ የምትሸምት ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ በዜጎቿ ላይ የተፈጠረውን የኑሮ ጫና ከፍተኛ በመሆኑ አሁንም መፍትሔ ያሻዋል። አንዱ መፍትሔ ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ ምርት እንዲኖር ማድረግ ነው።

ይህን ማድረግ ከተቻለ የዜጎችን የቀን ገቢንም ማሳደግ ይቻላል። ዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው እየጨመረ ሲሄድ፣ የሀገር ውስጥ ምርቶች ላይ ሲያተኩሩ፣ የማምረት አቅማቸውን በእጅጉ ሲያስተካክሉ፣ የማምረት ተነሳሽነታቸው ብቻም ሳይሆን አምርተው ለራሳቸውም ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉበት መንገድና ሁኔታ ይመቻቻል።

ሌላኛው መፍትሔ የማክሮ ኢኮኖሚን አሠራር በአግባቡ በመዘርጋትና በማስፈፀም እንዲሁም ሥራን በክህሎት መሥራት ከተቻለ ምርትን አሳድጎ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል። የብዙ ሀገራትን እጣ ፈንታ የቀየረው ማክሮ ኢኮኖሚ ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ከቀደመው በበለጠ መሥራት ሲቻል ነው።

አንድ ዜጋ ሥራ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በልምዱ፣ በእውቀቱ፣ በክህሎቱ ውጤት ማምጣት የሚችልበት ዘርፍ ላይ ሥራ ሲያገኝና ሲሰራ ውጤታማ ሆኖ የተሻለ ምርት ማምረት ይችላል። የተሻለ ምርት ሲገኝ በሀገሪቱ ያለውን ፍላጎት ማርካት የሚችል ምርት ሀገሪቱ እያቀረበች ነው ማለት ነው።

የተሻለ ምርት አምራች የሆነ ዜጋ የተሻለ ገቢ ያገኛል። የተሻለ ገቢ አለው ማለት ደግሞ ምርትን መጠቀም የሚችል ዜጋ አለ ማለት ነው። በዚህም አቅርቦትና ፍላጎት ይጣጣማል፤ ምርት እንዲትረፈረፍ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በመሆኑም በምርታማነት ላይ በተለይም በስንዴ እርሻ ላይ የተጀመረውን እንቅስቃሴ ወደ ሌሎች የምግብ ምርቶች ማስፋትና የገበያውን ሥርዓት ማስተካከል ለነገ የሚባል ሥራ አይደለም።

ባለፈው ወር ተስፋ የታየበትን የዋጋ ግሽበት ላይ የታየውን መሻሻል የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ጠንካራ ምርታማነትን በሥርዓት ማስኬድ ያስፈልጋል። ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ገበያ ላይ የሚቀርብበትን መንገዶች ምቹ ማድረግ ደግሞ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# ሲቢኢ ብር ፕላስ- ለቀልጣፋና ምቹ የክፍያ አገልግሎት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ዲጂታል ክፍያ ከጥሬ ገንዘብ ልውውጥ በመውጣት በክፍያ ካርድ፤ ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ፤ ገንዘብ በራሳቸው በሚከፍሉ ማሽኖች (ኤ ቲ ኤም)፣ ገንዘብ በሚያስተላልፉ ማሽኖች፣ በሞባይል ስልክ እና በመሳሰሉት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ገንዘብን ማስተላለፍ እና ክፍያ መፈፀም ማለት ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ያብራራሉ።

በዚህ የክፍያ ሥርዓት የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠንም በኢትዮጵያ በሁለትና ሶስት እጥፍ እያደገ መምጣቱንም መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም በአሁኑ ወቅት የሞባይል ግብይት ከፍተኛ እድገት ማስመዝገብ እንደቻለ ያመለክታሉ። ይህንን ተከትሎ መንግሥት የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት አካታችና በኃላፊነት ስሜት የሚመራ ሥነ ምህዳር እንዲኖረው የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ማዘጋጀቱ ይታወቃል። ስትራቴጂው የተዘጋጀው አካታችና በኃላፊነት ስሜት የሚተገበር የዲጂታል ክፍያ ሥነ ምህዳር መገንባት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ኢኮኖሚ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ሲሆን፣ በተጨማሪም አስቻይ ሁኔታን በመፍጠር በኩል እምነት በመታመኑ ነው።

የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን መተግበር ግልጽነትና ውጤታማነትን ከማስፈን፣ የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ፣ የፋይናንስ አካታችነትና ሁሉን አቀፍ እድገት ከማምጣት አኳያ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል ተብሎ ይታመናል።

በጥሬ ገንዘብ መጠቀምን በመተው ወደ ዲጂታል አማራጭ መሄድ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ያግዛል፣ የሕዝቦችን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል አጋጣሚዎችንም ይፈጥራል። የዲጂታል ክፍያ ስትራቴጂ ሰነዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክፍያ ሥነ-ምህዳሩን በማዘመን ውስን የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ያለውና የፋይናንስ አካታችነቱ የጎለበተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፍኖተ ካርታ በመሆን ያገለግላል።

በኢትዮጵያ የዲጂታል ዘዴዎችን ተጠቅሞ የክፍያ ሂደትን ለማቀላጠፍ በሚደረጉ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል። ለዚህም መንግሥት የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባትና ቁልፍ የሆነውን የዲጂታል ፋይናንስ ሥርዓት በማዘመን መመሪያና ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ አስቻይ ሁኔታዎች መፍጠሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

አሁን እየተሰራበት ያለው የወረቀት ገንዘብ ልውውጥ ባለበት መቀጠል እንደማይቻል ይታመናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአጠቃቀም ምቹ ቀላል፣ ቀልጣፋና ፈጣን የሆነውን የኦንላይን ክፍያ ድርጅቶች ተግባራዊ እያደረጉ መምጣታቸውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ከአካውንት ወደ አካውንት፣ ወደ ዋሌት እና ወደ ሌሎች ባንኮች ገንዘብ ማስተላለፍና በጥቅሉ የኦንላይን ባንኪንግ ሥርዓትን በመዘርጋት በኩል ከሚጠቀሱ ተቋማት መካከልም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይጠቀሳል። በሲቢኢ ብር አገልግሎቱ በስፋት የሚታወቀው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገልግሎቱን በማስፋት ቀልጣፋ እና ለአገልግሎት ምቹ የሆነውን ሲቢኢ ብር ፕላስን ደግሞ ይዞ መጥቷል።

ባንኩ ሲቢኢ ብር ፕላስ (CBEBirr Plus) በሚል በአዲስ መልክ አሻሽሎ ያቀረበውን የሲቢኢ አገልግሎት ደንበኞች መተግበሪያውን በማውረድ በቀላሉ መጠቀም እንደሚችሉም ባንኩ አስታውቋል። ባንኩ ሲቢኢ ብር ፕላስን በቅርቡ በይፋ ሥራ ባስጀመረበት ወቅት እንዳስታወቀው፤ የሲቢኢ ብር ተጠቃሚዎች ቁጥር ከአስራ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ ደርሷል።

ባንኩ እንዳስታወቀው፤ የሲቢኢ ብር አገልግሎትን በሰኔ 2009 ዓ.ም እንደ አንድ ዲጂታል የባንክ አገልግሎት አማራጭ አድርጎ የጀመረ ሲሆን፤ አገልግሎቱን በየጊዜው በማሻሻል




የተጠቃሚዎችን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሳደግ ችሏል።

ባንኩ በይፋ ሥራ ያስጀመረው 'የሲቢኢ ብር ፕላስ' መተግበሪያ በርካታ አገልግሎቶችን በማካተት ለአጠቃቀም ቀላል እና ምቹ እንዲሁም ቀልጣፋ ተደርጎ ተሻሽሎ የቀረበ ነው።

ሲቢኢ ብር ፕላስ መደበኛ አካውንትን ከሲቢኢ ብር ጋር ማስተሳሰር የሚያስችል በመሆኑ በቀላሉ ገንዘብ ወደ ሲቢኢ ብር መሳብ፣ የነዳጅ ክፍያን መፈጸም፣ ገንዘብ ለመላክ፣ ማንኛውንም የግዢ ክፍያ ለመፈጸም፣ የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችን መፈጸም፣ የኮንዶሚኒየም ብድር ክፍያ መፈጸም፣ የአየር ሰዓት ጥቅል አገልግሎት መግዛት ያስችላል።

ሲቢኢ ብር በሞባይል ገንዘብ ንግድ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የተሰለፈና በዋሌት ቢዝነስ ወደ ገበያ የመጣ ሲቢኢ ብር የዲጂታል ሶሉሽን ምርት ሲሆን፣ ሲቢኢ ብር የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን እያለፈ የመጣ ሲሆን፤ የገበያ ድርሻውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ፕላት ፎርም ወይም መተግበሪያ ነው። በተለይም በአንዳንድ መስኮች የገበያ ድርሻው በሀገሪቱ የዘርፉ ገበያ እስከ 90 በመቶ የደረሰ ግዙፍ የቴክኖሎጂ አማራጭ ነው። ይህ ተሻሽሎ የቀረበው ሲቢኢ ብር አሁን ላይ ከመደበኛ አካውንት ጋር በመተሳሰር በርካታ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰው ኃይል ምክትል ፕሬዚዳንትና የፕሬዚዳንቱ ተወካይ አቶ ኤፍሬም መኩሪያ እንዳሉት፤ ተሻሽሎ የቀረበው ሲቢኢ ብር በርካታ አዳዲስ አገልግሎቶችን የሚሰጥ፣ የደንበኞችን ጊዜ የሚቆጥብና ምቾታቸውን የሚጠብቁ አማራጮችን ይዞ የቀረበ ነው። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቀዳሚ ከሆነባቸው አገልግሎቶች መካከል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ይጠቀሳል። በዚህ አገልግሎትም የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት ያደረጉና በየዘመኑ ሥራ ላይ የዋሉ የባንክ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ያዋሉ የባንክ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል።

ባንኩ በኢንተርኔት፣ በሞባይል፣ ካርድ ባንኪንግ፣ በሞባይል መኒና የዲጂታል ባንኪንግ ክፍያዎችን ተደራሽ በማድረግ በየጊዜው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች እያሳደገ መጥቷል። አሁን እየቀረበ ባለው የአገልግሎት ምቹነትና አስተማማኝነት የተነሳ የደንበኞችን ቁጥር እያሳደገ መምጣት ችሏል።

የደንበኞች ቁጥር መጨመር ብቻም ሳይሆን፤ በዲጂታል አማራጮች አማካኝነት የሚፈጸመው የገንዘብ ዝውውርና የክፍያ መጠን በእጅጉ እያደገ መጥቷል። በመሆኑም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በባንኩ ከተፈጸመው ከአንድ ነጥብ አምስት ስድስት ቢሊዮን የሚበልጥ የገንዘብ ዝውውር ወይም 31 ትሪሊዮን የሚጠጋ ብር ውስጥ በዲጅታል ባንኪንግ አማራጮች አማካኝነት የተፈጸመው 72 በመቶ ድርሻ ይዟል።

ከዲጂታል ባንኪንግ አማራጮች መካከል የአብዛኛውን ማህበረሰብ አቅምና ፍላጎት ያማከለውና በርካታ አገልግሎቶች የቀረቡበት የሲቢኢ ብር የተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም ሞባይል መኒ አገልግሎት አንዱ መሆኑን አቶ ኤፍሬም ጠቅሰው፣ ከዛሬ ሰባት ዓመት አስቀድሞ የቀረበው ይህ አገልግሎት በተለይም እንደ ውሃ፣ የኤሌክትሪክና ሌሎች መሰል የክፍያ አገልግሎቶችን ደንበኞች ባሉበት ቦታ ሆነው መክፈል እንዲችሉ በማድረግ ተመራጭ መሆን ችሏል ብለዋል።

ይህም የበርካታ ደንበኞችን ወጪ፣ ጊዜና ድካም በማስቀረት አስተማማኝ አገልግሎት ማቅረብ አስችሏል ሲሉም ተናግረው፣ በዚሁ ቀልጣፋና ለአጠቃቀም ምቹ በሆነው አገልግሎት ከባንኩ ጋር አብረው የሰሩ ተቋማት የአገልግሎት ገቢያቸውን በአግባቡ መሰብሰብ እንዲችሉ በማድረግ ትልቅ አቅም እንደፈጠረላቸውም አስታውቀዋል።

የሲቢኢ ብር አገልግሎት ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በኋላ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ተጠቃሚዎች እንደነበሩት ያስታወሱት አቶ ኤፍሬም፤ በቀጣይ ዓመት 189 ከመቶ የሚደርስ አፈጻጸም በማስመዝገብ የተጠቃሚዎቹን ቁጥር ከስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ማድረስ እንደቻለ ተናግረዋል። በዚህ ጊዜ ሲሰጡ የነበሩ አገልግሎቶችና በሲቢኢ ብር አማካኝነት ይፈጸሙ የነበሩ ግይብቶችና የገንዘብ ዝውውሮች በዓይነትና በመጠን ከፍተኛ ለውጥ ማምጣታቸውንም አስታውቀዋል። በመሆኑም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ማጠቃለያ የሲቢኢ ብር ተጠቃሚ ደንበኞች ብዛት ማለትም አገልግሎቱን በተከታታይ የተጠቀሙ ደንበኞችን ቁጥር በእጥፍ በማሳደግ 12 ሚሊዮን ማድረስ እንደተቻለም ተመላክቷል።

የባንኩ ምክትል ፕሬዚዳንት እንዳስታወቁት፤ የጥሬ ገንዘብ አልባ ግብይትን ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ለማድረስ የሲቢኢ ብር አገልግሎት ከፍተኛ ሚና መጫወት ባንኩ በጽኑ ያምናል። በአሁኑ ወቅትም የደንበኞችን ፍላጎት በማጥናት እርካታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ሊያደርስ የሚችል የአገልግሎት ማሻሻያን ይዞ ቀርቧል። ይህ የአገልግሎት ማሻሻያም ከUSSD በተጨማሪ በሞባይል መተግበሪያ አማካኝነት የሲቢኢ ብር አገልግሎት የሚሰጥበት ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ይሰጡ የነበሩ የክፍያ የገንዘብ ዝውውር አማራጮችን በማስፋት የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም ሲቢኢ ፕላስ ብር ይዟቸው የመጣቸው አማራጮች ከነባር ደንበኞች በተጨማሪ አዳዲስ ደንበኞች ጭምር እንዲጠቀሙ የሚጋብዝ ቀላል፣ ፈጣንና ምቹ አገልግሎት ነው።

ባንኩ ሲቢኢ ፕላስን ይፋ ባደረገበት ወቅት ከተገኙ የሥራ ኃላፊዎች መካከል የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደር /ኢንሳ/ ዋና ዳይሬክተር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይዘሪት ትዕግስት ሀሚድ አንዷ ናቸው። እሳቸው እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጅታል ባንኪንግ ሥርዓትን በመሪነት የያዘና የተለያዩ ማሻሻያዎችን አድርጓል፤ መተግበሪያዎችን ሲያስተዋውቅ ቆይቶ፣ በዚህም ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።

ዋና ዳይሬክተሯ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሁንም በርካታ አገልግሎቶችን በሲቢኢ ብር ፕላስ ለደንበኞቹ ይዞ ቀርቧል። ይህም በዲጂታል ቴክኖሎጂው ያለና በየጊዜው ማሻሻልን የሚፈልግ ዘርፍ በመሆኑ ነው። ለዚህም ነው ባንኩ በተቋሙ ውስጥ በሚያደርጋቸው ዘመናዊ የትራንስፎርሜሽን ሥራዎቹ ጭምር አንጋፋና ግንባር ቀደም ተቋም ሲሆን፣ ይህንንም በአዳዲስ አገልግሎቶቹ እያስመሰከረ ይገኛል። በአሁኑ ወቅትም የትራንስፎርሜሽኑ አካል የሆነውን የዲጂታል አክሰሰቢሊቲ ስኬት ጉዞውን እያስቀጠለ ለመሄዱ ወደ ሥራ ያስገባው የሲቢኢ ብር ፕላስ ማሻሻያ አንዱ ማሳያ ነው።

ባንኩ እንደ አንድ የፋይናንስ ተቋም የዲጂታል አገልግሎትን ለሁሉም ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ የሚያቀርበውን ዲጂታል አገልግሎት በየጊዜው በማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ባንኩ አዲስ ያቀረበው የሲቢኢ ብር ፕላስ መተግበሪያም በሚገባ በባለሙያ ተፈትሾ ደህንነቱና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ መተግበሪያው በውስጥ አቅም የተሠራ ነው። ይህን የተቋሙን ጥረት አድንቀው፣ በሥራው ለተሳተፉ ሁሉ ምስጋና በማቅረብ የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክት አስተላልፈዋል።

አዲስ የተሻሻለው የሲቢኢ ብር ፕላስ (CBE-Birr Plus) መተግበሪያ ነባሮቹን አገልግሎቶች በማሻሻል እና አዳዲስ አገልግሎቶችን በመጨመር ለአጠቃቀም ቀላል እና ምቹ ሆኖ የቀረበ ሲሆን፤ ደንበኞች አገልግሎቱን ለማግኘት በራሳቸው መመዝገብ የሚያስችላቸው እንደሆነ በወቅቱ ተመላክቷል።

ደንበኞች ተጨማሪ የሲቢኢ ብር ፕላስ አገልግሎቶችን ለመጠቀም ከመደበኛው ሂሳብ ጋር በማስተሳሰር አገልግሎቶቹን ማግኘት እንደሚችሉም በመድረኩ ተጠቁሟል። አገልግሎቱም ደንበኛው ቅርንጫፍ መሄድ ሳያስፈልገው ሲቢኢ ብርን ከመደበኛ ሂሳቡ ጋር በማስተሳሰር ገንዘብ ለመሳብ፣ ነዳጅ ለመክፈል፣ ገንዘብ ለመላክ፣ የተለያዩ የቢል ክፍያዎችን ለመፈጸምና የኮንዶሚኒየም ብድር ለመክፈል፣ እንዲሁም ወደሌሎች ባንኮች ብር መላክ ለመክፈል የሚያስችል ቀላል ቀልጣፋና ምቹ ሆኖ የቀረበ መሆኑም ተጠቁሟል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## መካከለኛው መደብ ጭቁን ወይስ ሥልጡን?

ዋለልኝ አየለ

አንዳንድ ሰዎች የአንድን ሰው አለመሰልጠን ለመግለጽ ‹‹ዝግመተ ለውጡን ያልጨረሰ›› እያሉ ሲሳደቡ እንሰማለን። ስድቡ ነውር መሆኑ እንዳለ ሆኖ ልብ ያልተባለው ነገር ግን የተጠየቅ ስህተት ያለበት መሆኑ ነው። ዝግመተ ለውጥ አያልቅም። የአሁኑ ሆሞ ሳፒያንስ ከአንድ ሺህ፣ ሁለት ሺህ፣ ሦስት ሺህ.... አሥራ ምናምን ሺህ ዓመታት በኋላ ሆሞ ሀቢለስ፣ ሆሞ ኢሬክተስ እንደምንለው የቀደሙ ዝግመተ ለውጥ አይነቶች ይሆናል። ይህ አሁን የምንኖረው ሕይወት (የአውሮፓዎችን ጨምሮ) ‹‹የሰው ልጅ እንዲህም ይኖር ነበር?›› እየተባለ እንደ ኋላቀር የሚታይ ይሆናል።

ይሄ ማለት አሁን ያለነው የሰው ልጆች ሆሞ ሀቢለስን እና ሆሞ ኢሬክተስን እያየን ‹‹እንዴት የሰው ልጅ ከዚህ ደረጃ ተነስቶ እዚህ ላይ ደረሰ?›› እያልን እንደምንገረመው ሁሉ ከአሥራ ምናምን ሺህ ዘመናት በኋላ የሚኖረው የሰው ልጅ ይህን አሁን የተገረምንበትን ቴክኖሎጂ ምናልባትም እኛ የድንጋይ ዘመንን እንደምናየው ሊያየው ይችላል። አስባችሁታል ‹‹ድሮ የሰው ልጅ አውሮፕላን በሚባል ነገር በሰማይ ላይ ይሄድ ነበር›› እያሉ እንደ ኋላቀር ሲያዩት?

በፈረንሳይ ፓሪስ እየተካሄደ ያለው የኦሊምፒክ ውድድር ከመክፈቻው ጀምሮ ብዙ አስገራሚ ነገሮችን አሳይቶናል። በተለይም መክፈቻው ላይ ብዙ ነውር እና ፀያፍ ነገሮች ታይተዋል። የሥልጣኔ ጣሪያ ላይ ናቸው በሚባሉ ሀገራት እንዲህ አይነት ነገሮች በተደጋጋሚ እየታዩ ነው። ለመሆኑ መሠልጠን ማለት ምን ማለት ይሆን? በልማድ በተሰጠው የሰለጠኑ እና ያልሰለጠኑ ብያኔ መሰረት እስኪ ልዩነታቸውን እናነፃፅር።

ከመሰልጠን አንፃር የሰው ልጅ መደብ አለው። አንድ የሚገርመኝ ነገር ግን እጅግ በጣም የሰለጠኑ እና እጅግ በጣም ኋላቀር ናቸው የሚባሉት ወገኖች ሕይወት የሚመሳሰለው ነገር ነው። ጫፍ እና ጫፍ ያሉት እንደገና ይመሳሰላሉ። ከሁለቱ የሚርቀው የመካከለኛው መደብ ነው፤ የመካከለኛው መደብ በሁለቱም አኗኗርና ድርጊት ይገረማል። ሲጀመር ኋላቀርና የሰለጠነ ብሎ የፈረጀውም የመካከለኛው መደብ ሳይሆን አይቀርም። በእርግጥ በጣም የሰለጠኑትም እንደ አፍሪካ ሀገራት ያሉትን በኋላቀርነት ይፈርጃሉ። ልብ ብለን ካየነው ግን መሰልጠን የቱ ነው? ኋላቀርነትስ የቱ ነው? የሚለው ማለቂያ የለሽ ጥያቄ ያስነሳል።

በተለምዶ የተሰጠውን ብያኔ ይዘን የላይኛው መደብ እና የታችኛው መደብ ያላቸውን መመሳሰል ልብ እንበል። ለምሳሌ፤ ከሥልጣኔ የራቁ ናቸው፣ እጅግ በጣም ኋላቀር ናቸው የሚባሉት አካባቢዎች ራቁታቸውን የሚሄዱ ናቸው። ምንም ልብስ የሚባል ነገር ሰውነታቸውን የማይነካው ሀገራትና አካባቢዎች (ለምሳሌ ታንዛኒያ ውስጥ እና አማዞኒያ አካባቢ) አሉ። እነዚህ የተጠቀሱት ጭራሹንም ምንም አይነት ልብስ የማይነካቸው ናቸው። የእነዚህ ወገኖች ሕይወት የሚገለጸው ገና ልብስ የመልበስ ደረጃ ላይ ስላልደረሱ ነው በሚል ነው። አኗኗራቸውም የዘመኑ መለያ የሆኑ መገልገያዎች የሌሉበት ስለሆነ በኋላቀርነት ተይዟል።

በተቃራኒው ደግሞ የሥልጣኔ ጣሪያ ላይ ናቸው በሚባሉት ሀገራት እየሆነ ያለውን ነገር ልብ እንበል። ራቁት መሆን በድጋሚ ፋሽን እየሆነ ነው። ለምሳሌ እንደ ኒዮርክ ባሉ ሀገራት ሙሉ ራቁት የሚኮንባቸው ሪዞርቶች አሉ። ራቁት ማለት ሀፍረተ ሥጋቸውን እንኳን የምትሸፍን እራፊ ጨርቅ ሳይኖር ሙሉ ራቁት ማለት ነው። በመዲናችን አዲስ አበባም ከሰለጠኑት ሀገራት የተኮረጀ የሥልጣኔ መገለጫ ነው ተብሎ የራቁት ጭፈራ ቤቶች ተስፋፍተዋል። የፈረንሳዩ ቴሌቪዥን ፍራንስ 24 ሀፍረተ ሥጋቸው እንዳይታይ በማድረግ ሪዞርቶች ውስጥ ስለሚደረገው የሙሉ ራቁት መዝናናት ዘገባ ሰርቶ ነበር። አስተያየት ሰጪዎች ልብስ እንደማያስፈልግ ሲናገሩ ነበር። የሰጡት አስተያየት ሲጠቃለል፤ ሰውን ከሰው ያበላልጣል፣ ደረጃ ይፈጥራል፣ የሰው ልጅ የተፈጠረው ራቁቱን ነውና ነፃ መሆን አለበት.... የሚሉ ናቸው። ይህ እብደታቸው በራሳቸው ሀገርም ቢሆን አልተወደደም። የሁለቱ (የሰለጠኑ የተባሉትና ያልሰለጠኑ የተባሉት) ራቁትነት ግን የሚታይበት አተያይ ይለያያል። ግን ምን ልዩነት ነበረው?

ሌላው መለያ ደግሞ ሃይማኖት ነው። እጅግ ኋላቀር ናቸው፣ አልሰለጠኑም የሚባሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች (ጎሳዎች) የተደራጀና የሚታወቅ ተቋማዊ ሃይማኖት የላቸውም። የሚኖሩት በደመ ነፍስ ነው። በተመሳሳይ እጅግ በጣም የሰለጠኑ ናቸው የሚባሉትም ሃይማኖት የላቸውም፤ እነርሱም የሚኖሩት የዕለት የዕለቱን ነው። ተመራምረው ተመራምረው የፍልስፍና ጥግ ላይ ደረሱ የሚባሉ ሰዎች ልክ አልሰለጠኑም እንደሚባሉት አካባቢዎች ሁሉ ውስብስብ ነገር አያበዙም። የእነርሱ ሲሆን ግን እንደ ፍልስፍና ይቆጠራል።

ባህልና ወግን ከተመለከትንም ተመሳሳይ ነው። እጅግ ኋላቀር ናቸው የሚባሉ ወገኖች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ‹‹ይህ አይደረግም፣ ይህ ነውር ነው...›› የሚባል ነገር ብዙም የለም። በአብዛኞቹ የዓለም ሀገራት ባህል እንደ ነውር የሚታየው ወሲብ ራሱ እንደ ነውር የማይታይባቸው ጎሳዎች አሉ። እንዲያውም በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ወሲብ ነውር የሆነው ከአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት በኋላ ነው የሚሉ መረጃዎችም አሉ። አውሮፓውያን ቀድመው ሰልጥነው እንደ ነውር ማየት ጀምረው ነበር ማለት ነው። በኋላ ደግሞ እንደገና ወደኋላ ተመልሰው በግልጽ ውይይት እንዲደረግበት የሚያስተምሩም እነርሱ ሆኑ።

ልክ እንደዚህ ሁሉ በጣም የሰለጠኑ ናቸው በሚባሉት ሀገራትም ‹‹ይህ አይደረግም፣ ይህ ነውር ነው....›› የሚባል ነገር የለም። በባህልና ወግ በግልጽ የማይነገሩ ነገሮችን ሕጋዊ እስከማድረግ ደረሱ። ሃይማኖትና ባህል የሚባሉ ነገሮች ብዙም ቦታ የማይሰጣቸው ሆኑ። ጭራሽ ይባስ ብለው እንስሳዊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ማስተዋወቅ ጀመሩ። ነፃ አስተሳሰብ፣ ነፃ ሕይወት፣ ነፃ እንቅስቃሴ የሚባሉ ነገሮችን እንደ ዘመናዊነት ማየት የተጀመረው የሰለጠኑ ናቸው በሚባሉት ሀገራት ነው። እነሆ ከእነርሱ በመኮረጅ ጥንት ነፃ የነበሩ ሰዎች እንደገና ደግሞ ወደ ነፃነት እየሄዱ ነው ማለት ነው።

በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለው መደብ ግን ብዙ የሚያነውራቸው ነገሮች አሉት። የሞራል ጥግ ላይ ነኝ ብሎ ያምናል። ያልሰለጠኑ ናቸው የሚባሉ ጎሳዎች ራቁታቸውን መሆናቸውን ከኋላቀርነት ጋር ያያይዘዋል። ሆኖም ግን እነርሱ ይሻሉታል። የሥልጣኔ ጣሪያ ላይ ያሉ ሀገራት የሚያደርጉትን ደግሞ ‹‹ሰይጣናዊ ድርጊት›› በማለት አምርሮ ያወግዘዋል። ይህ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በአሜሪካና አውሮፓ ሀገራትም አከራካሪ ነው፤ በራቁትና በልቅነት የሚያምኑት ሁሉም አይደሉም፤ በጣም ጥቂቶች ናቸው። መካከለኛው መደብ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ሞራል... የሚባሉ ነገሮች ይገዙታል።

እንግዲህ ሰሞኑን በፈረንሳይ ፓሪስ የኦሊምፒክ ውድድር እየተካሄደ ነው። ከመክፈቻው ጀምሮ ብዙ አስገራሚ ነገሮች ታይተዋል። ብዙ ነውር የሆኑ ነገሮች ታይተዋል። ብዙ የሀገራችን ሰዎች ‹‹መሰልጠን እንዲህ ከሆነ...›› እያሉ ነው። ያንን ድርጊት ‹‹ያልሰለጠኑ›› ናቸው የተባሉ ሀገራት አድርገውት ቢሆን ኖሮ ከኋላቀርነት ጋር ይያያዝ ነበር። ግን ያደረጉት የሥልጣኔ መዳቢዎች ናቸው። ስለዚህ እነርሱ ሲያደርጉት ለምን ኋላቀርነት አይባልም?

ለመሆኑ ግን የመካከለኛው መደብ ሥልጡን ነው ወይስ ጭቁን የሚባለው? የእነርሱ ልቅነት ነፃነት ከተባለ የመካከለኛው መደብ ሥነ ሥርዓት ጭቆና ሊባል ነው? ቅጥ ያጣ ሥልጣኔ ወደ ድንጋይ ዘመን የሚመልስ ከሆነ ይህ አይነት ሥልጣኔ ይቅርብን!

# ዓለም አቀፍ



## በኢራቅ የሚገኘው የአሜሪካ ወታደራዊ ጣቢያ የሮኬት ጥቃት ተፈጸመበት

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኢራቅ የሚገኘው የአሜሪካ ወታደራዊ ጣቢያ የሮኬት ጥቃት ተፈጸመበት።

በሮኬት ጥቃቱ በጥቂቱ አምስት ወታደሮች መቁሰላቸም ነው የተነገረው።

በምዕራባዊ ኢራቅ በሚገኘው ወታደራዊ ጣቢያ ላይ ሁለት ሮኬቶች መተኮሳቸውን የኢራቅ ባለስልጣናትን ጠቅሶ ሬውተርስ ዘግቧል።

ጥቃቱ አሜሪካ በኢስማኤል ሃኒየህ ግድያ በተዘዋዋሪም ቢሆን እጇ አለበት ያለችው ኢራን እወስደዋለሁ ካለችው የአጸፋ ርምጃ ጋር ስለመያያዙ ግን አልታወቀም።

ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የአሜሪካ ባለስልጣን በኢራቅ በተፈጸመው ጥቃት ጉዳት ከደረሰባቸው ውስጥ አንዱ ለህይወቱ አስጊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝና የቆሰሉት ቁጥርም ከፍ ሊል እንደሚችል ይጠበቃል ብለዋል።

ጥቃቱ እስራኤል በሊባኖስና ኢራን መዲናዎች የሄዝቦላህና ሃማስ ከፍተኛ መሪዎችን መግደሏን ተከትሎ ቴህራን እወስደዋለሁ ያለችው የበቀል እርምጃ ዋሽንግተንንም ሊያካትት እንደሚችል አመላክቷል።

የጋዛ ጦርነት ከተጀመረ አንስቶ በኢራቅ፣ ሶሪያ፣ የመንና ሊባኖስ የሚገኙና ኢራን ድጋፍ የምታደርግላቸው ታጣቂዎች በአሜሪካ ወታደራዊ ይዞታዎች ላይ ጥቃት ሲፈጽሙ መቆየታቸው ይታወሳል።

ተጨማሪ የጦር መርከቦችና ተዋጊ ጄቶችን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እልካለሁ ያለችው ዋሽንግተን ከቴህራን ጋር መልካም ግንኙነት ያላት ባግዳድ ውጥረቱን በማርገብ ሂደት እንድታግዛት ጠይቃለች።

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንም ለኢራቁ ጠቅላይ ሚኒስትር ሞሀመድ ሺያ አል ሱዳኒ ደውለው ቴህራንን እንዲያግባቡ ጠይቀዋቸዋል ነው የተባለው።

በቀጣናው በልዩነት የኢራንም የአሜሪካም አጋር በሆነችው ኢራቅ 2 ሺህ 500 የአሜሪካ ወታደሮች ይገኛሉ።

የእስራኤልና ሃማስ ጦርነት ከተጀመረ አንስቶ በአሜሪካ ወታደሮች ላይ ያነጣጠሩ ተደጋጋሚ ጥቃቶች ተፈጽመዋል።

ባግዳድ የጥቃት ማዕከል የሆኑት የአሜሪካ ወታደሮች ከመጪው መስከረም ወር ጀምሮ ከሀገሪቱ እንዲወጡና በአንድ ዓመት ወታደራዊ ጣቢያው እንዲዘጋ ትፈልጋለች ተብሏል።



## ኢራን ቀጣናዊ ውጥረት እንዲፈጠር ባትፈልግም፣ እስራኤልን ግን “እቀጣለሁ” አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኢራን ቀጣናዊ ውጥረት እንዲፈጠር ባትፈልግም፣ እስራኤልን ግን “እቀጣለሁ” አለች።

ኢራን ቀጣናዊ ውጥረቱን የማባባስ ፍላጎት ባይኖራትም፣ ተጨማሪ አለመረጋጋትን ለማስቀረት እስራኤልን መቅጣት ያስፈልጋል ብለው እንደሚያምኑ የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ተናግረዋል።

ቃል አቀባዩ ይህን ያሉት የሀማስ የፖለቲካ መሪ እስማኤል ሀኒየህ እስራኤል ሳታደርሰው አትቀርም በተባለው ጥቃት በኢራን ዋና ከተማ መገደሉን ተከትሎ ነው።

“ኢራን በቀጣናው መረጋጋት እንዲፈጠር ትፈልጋለች፤ ነገር ግን ይህ የሚሳካው ተንኳሹን በመቅጣት እና ጽዮናዊው አገዛዝ ጥቃት መፈጸም እንዳይችል ማድረግ ሲቻል ነው” ያሉት ቃል አቀባዩ ናሰር ከናኒ ኢራን የአጸፋ ምላሽ መስጠቷ አይቀሬ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በቀጣናው መረጋጋት ማምጣት ስላልቻለ በተንኳሹ ላይ የሚደረገውን ቅጣት መደገፍ አለበት ያሉት ካናኒ፤ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገውን ድጋፍ እንድታቆም ጥሪ አቅርበዋል።

የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቴህራን የሚገኙትን አምባሳደር እና የተልእኮ ኃላፊ ከተጠባባቂው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ ባግሪ ካኒ ጋር ተሰብስበው የኢራን ርምጃ አይቀሬነት ተነግሯቸዋል።

ከናኒ እንዳሉት፤ ኦርጋናዜሽን ኦፍ እስላሚክ ኮኦፕሬሽን በሀኒየህ ግድያ ዙሪያ ውይይት እንዲያደርግ በኢራን ጥያቄ መሰረት በመጪው ረቡዕ አስቸኳይ ስብሰባ ያካሂዳል።

ኢራን እና አጋሮቿ ሀማስ እና ሄዝቦላን ጨምሮ በሀኒየህ ላይ ግድያ የፈጸመችው እስራኤል ነች የሚል ክስ እያሰሙ ናቸው።

ይህ ግድያ 11ኛ ወሩን ያስቆጠረው የእስራኤል-ሀማስ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ በሀማስ መሪዎች ላይ ከተፈጸሙት ግድያዎች ውስጥ አንዱ ነው።

የእስራኤል ባለስልጣናት እስካሁን ለግድያው ኃላፊነት አልወሰዱም። የኢራኑ አብዮታዊ ዘብ ጠባቂ ከፍተኛ አዛዥ የሆኑት ሆሴን ሳላሚ ከትናንት በስቲያ “ጊዜው ሲደርስ እስራኤል ቅጣቷን ትቀበላለች” ሲሉ ዝተዋል።

## ባለውለታዎቻችን

# የሜክሲኮ ኦሎምፒክ ድምቀት

- ሻምበል ማሞ ወልዴ



ክብረአብ በላቸው

በስፖርት፤ በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በታሪክ፣ በሳይንስ ኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ እንቁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህ የሀገር ባለውለታ ግለሰቦች መካከል ኢትዮጵያ በስፋት በምትታወቅበት የአትሌቲክስ ስፖርት በተለይ በረዥም እርቀት አትሌቲክስ በርካታ ውድድሮችን በማሸነፍ ታሪክ የሠራውና የሀገሩን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም መድረክ ማውለብለብ የቻለው አንጋፋው አትሌት ሻምበል ማሞ ወልዴ አንዱ ነው።

ማሞ የተወለደው በ1932 ዓ.ም ላይ ከአዲስ አበባ 60 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ አዳአ ከተማ በምትገኘው ድሪጂሌ መንደር ነበር። ከትውልድ መንደሩ ተነስቶ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ በውትድርና የመሥራት እድል አግኝቶ በክቡር ዘበኛ በ19 ዓመቱ ተቀጠረ።

ለሁለት ዓመታት በውትድርና እየሰለጠነ ጎን ለጎን ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶ 21 ዓመት ሲሞላው የክቡር ዘበኛው 2ኛ ባታሊዮን በሰላም አስከባሪነት ወደ ኮሪያ ሲዘምት አብሮ ዘመተ። በክቡር ዘበኛ ወታደርነት ኮሪያ በዘመተው የሰላም አስከባሪ ጦር እና በሌሎች ሥራዎች ለ2 ዓመታት በማገልገል ልዩ ምስጋና አግኝቷል። በውትድርና ውስጥ ሆኖ ትኩረትን ወደ ስፖርቱ ማድረግ የጀመረው ከኮሪያ መልስ ነው። በተለያዩ የሀገር ውስጥ የአትሌቲክስ ውድድሮች ለመግባት የውትድርና አቋሙ ያገዘው ሲሆን በየጊዜው በሚደረጉ ብሔራዊ ሻምፒዮናዎች ይሳተፍም ነበር።

የኢትዮጵያና የሻምበል ማሞ የመጀመሪያ ኦሎምፒክ በ1956 እኤአ ላይ በአውስትራሊያዋ ሜልቦርን ከተማ የተካሄደው 16ኛው ኦሎምፒያድ ኢትዮጵያ በኦሎምፒክ መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈችበት ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ቡድን በ8 ወንድ ኦሎምፒያኖች ብቻ የተገነባ ሲሆን በ29 ዓመቱ በእድሜ አንጋፋው የቡድኑ አባል ማሞ ነበር።

ሜልቦርን ላይ ኢትዮጵያ በታላቁ የኦሎምፒክ መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሳተፍ ሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት ጋና፤ ላይቤሪያና ደቡብ አፍሪካ ነበሩ። በዚያን ወቅት ባልተሟላ አደረጃጀት የተመሠረተው የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በሜልቦርን ኦሎምፒክ የሚሳተፉ የኢትዮጵያ ፈርቀዳጅ ኦሎምፒያኖችን የመለመለው ከጦር ኃይልና ከተለያዩ የስፖርት ክለቦች ነበር።

የክቡር ዘበኛ ወታደርና ስፖርተኛ የሆኖ ሻምበል ማሞ በተለያዩ የሀገር ውስጥ ውድድሮች የነበረው ልዩ ብቃትና ውጤታማነት በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የኦሎምፒክ ቡድን ሲመረጥ ብዙዎች በማራቶን ውድድር እንደሚሰለፍ ገምተው ነበር። ይሁንና የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ማሞን የመረጠው ደግሞ በ800 ሜትር፤ በ1500 ሜትር እና በ4X400 ሜትር እንዲወዳደር ነበር። ሻምበል ማሞ ወልዴ በዚህ የኢትዮጵያ ስፖርት አዲስ ምዕራፍ በመካከለኛ እና በአጭር ርቀት ለመሳተፍ ከበቁ የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ኦሎምፒያኖች አንዱ ለመሆን የቻለ ነበር።

ሻምበል ማሞ በዚህ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ኦሎምፒክ ተሳትፎው ለፍፃሜ ውድድሮች ባይበቃም በመካከለኛ ርቀት ፈር ቀዳጅ ኦሎምፒያን መሆኑ የሚጠቀስ ታሪኩ ነው። በ1960 እኤአ ላይ የጣሊያኗ ሮም ከተማ 17ኛውን ኦሎምፒያድ ስታዘጋጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሩጫ የተለያዩ የውድድር መደቦች ምርጥ ከሆኑ አትሌቶች አንዱ የነበረው ማሞ ወልዴ ለሁለተኛ ጊዜ በኦሎምፒክ መድረክ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው።

በክቡር ዘበኛ ከአበበ ቢቂላ ጋር በውትድርናውም በስፖርቱም የነበራቸው ጓደኝነት አነሳስቶት በኦሎምፒክ የማራቶን ውድድር መሮጥ ቢፈልግም አልሆነለትም።

ሻምበል ማሞ በሮም ኦሎምፒክ የሚሳተፍበት እድል ቢበላሽበትም ሀገሩን በሚያገለግልበት ኃላፊነት መሰማራቱ አልቀረም። የተባበሩት መንግሥታት ኮንጎ ላይ ባሰማራው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ጦር አባል ሆኖ ለ1 ዓመት ሀገሩን በውትድርና አገልግሏል።

በሮም ኦሎምፒክ የማሞ ወልዴ የቅርብ ጓደኛ፤ አጋር ወታደር እና ስፖርተኛ አበበ ቢቂላ በማራቶን ለአፍሪካ እና ለኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ የሆነ ድል ማስመዝገቡ ከፍተኛ መነቃቃት ፈጥሮ ነበር። ከአበበ የኦሎምፒክ የማራቶን ታላቅ ገድል በኋላ በ1964 እኤአ ላይ የጃፓኗ ቶኪዮ ከተማ 18ኛውን ኦሎምፒያድ ስታስተናግድ ለኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ቡድን በተለያዩ የአትሌቲክስ የውድድር መደቦች በተለይም በማራቶን ከፍተኛ ልምድ ያካበተው ማሞ ወልዴ፤ ለውጤታማነት ከተጠበቁ የኢትዮጵያ ኦሎምፒያኖች አንዱ ነበር።

ሮም ላይ በ10ሺ ሜትርና በማራቶን ውድድሮች ኢትዮጵያን በመወከል እንዲወዳደር ተመርጧል። ኢትዮጵያ በታሪክ ለ3ኛ ጊዜ በተሳተፈችበት የሮም ኦሎምፒክ ማሞ ሁለተኛውን የኦሎምፒክ ተሳትፎውን በ10ሺ ሜትር አድርጎ አራተኛ ደረጃ በማግኘት የዲፕሎማ ተሸላሚ ለመሆን በቃ።

1968 እኤአ ላይ 19ኛው ኦሎምፒያድ በሜክሲኮ ሲካሄድ ከአበበ ቢቂላ በኋላ ለሜዳሊያ ውጤት የኢትዮጵያ ብቸኛ ተስፋ ከፍተኛ ልምድ የነበረው ምርጥ ኦሎምፒያን በወቅቱ የመቶ አለቃ ማዕረግ የነበረው ማሞ ነበር። እንደ ቶኪዮ ኦሎምፒክ ሁሉ ሜክሲኮ ላይ በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ቡድን የተያዘው በ10ሺ ሜትር እና በማራቶን እንዲወዳደር ነው። ውጤታማ እንደሚሆንበት ከታመነው የማራቶን ውድድር አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በሜክሲኮ ኦሎምፒክ በመጀመሪያ በ10ሺ ሜትር ተወዳደረ።

ኬንያዊው ናፍታሌ ቴሞ በአጨራረስ ብልጠት አሸንፎ የወርቅ ሜዳልያውን ሲወስድ ማሞ በሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የቱኒዚያው መሃመድ ጋሃሚ በሶስተኛ ደረጃ ውድድራቸውን በመጨረስ የብርና የነሐስ ሜዳልያዎችን ተጎናፅፈዋል። ማሞ ወልዴ በሶስተኛ የኦሎምፒክ ተሳትፎው የመጀመሪያውን የኦሎምፒክ የብር ሜዳልያ ለመጎናፀፍ የበቃው በ29፡ 27.75 በሆነ ጊዜ ርቀቱን በመሸፈን ሲሆን ይህ ውጤት ለኢትዮጵያ የረጅም ርቀት ሩጫ ፈር ቀዳጅ ሆኖ መጠቀስ ያለበት ነው።

ሻምበል ማሞ በ10ሺ ሜትር የብር ሜዳልያው ከተጎናፀፈበት ድል በኋላ ግን ከአድካሚው ውድድር እፎይ የሚልበት ጊዜ አልነበረውም፤ ከሳምንት በኋላ በማራቶን ሲወዳደር የአበበን የድል ታሪክ መድገም እንደሚኖርበት የኢትዮጵያን ክብር የማስጠበቅ ኃላፊነት የእሱ መሆኑን በወቅቱ አሰልጣኝ የነበሩት አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባ ነገሩት። በሜክሲኮ ኦሎምፒክ በማራቶን ውድድሩ ላይ በሁለት ተከታታይ ኦሎምፒኮች ሁለት የወርቅ ሜዳልያዎችን በመጎናፀፍ የተደነቀውን አበበ ቢቂላን ለመፎካከር ከተሰለፉት የ44 ሀገራት አትሌቶች ውስጥ አንዱ ማሞ ነበር።

ሜክሲኮ ላይ ለሶስተኛ ጊዜ የኦሎምፒክ ማራቶንን እንደሚያሸንፍ የተጠበቀው አበበ ቢቂላ በህመም ውድድሩን አቋርጦ ለመውጣት ሲገደድ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም የስፖርት አፍቃሪዎች ልብ በሀዘን ተሰበረ።

አበበ 20ኛው ኪሎ ሜትር ላይ ውድድሩን አቋርጦ ከመውጣቱ በፊት ከማሞ ጋር በሩጫ ላይ ያደረጉትን ምክክር አሜሪካዊው ኦሎምፒያን ኬኒ ሞር ለራነርስ ዎርልድ በፃፈው መጣጥፍ ላይ እንዲህ ይላል፡-

**‹‹ሉታነት ማሞ‹‹ ሲል አበበ ተጣራ**

**‹‹ውድድሩን የምጨርስ አይመስለኝም።››**

**‹‹አንተ ግን ውድድሩን ማሸነፍ አስብህ››**

**‹‹አታሳፍረኝም መቼም‹‹ አለና አበበ ቢቂላ**

**በመጨረሻ ሩጫውን አቋረጠ ይላል።**

ማሞ ግን ከአበበ ጋር ካደረጉት ምልልስ በኋላ በከፍተኛ ሞራል መሮጡን ቀጠለ። ዱካውን በመከተል ተፎካካሪ የሆነው የኬንያው ናፍታሊ ቴሞ ነበር። የመጨረሻዎቹን የማራቶን ርቀቶችን ለመጨረስ ከሜክሲኮው ኦሎምፒክ ስታድዬም አካባቢ ሲደርሱ ማሞ ፍጥነቱን ጨምሮ አፈተለከና የአሸናፊነቱን ሪባን በጠሰ። በኦሎምፒክ ማራቶን ለኢትዮጵያ ሶስተኛውን ለራሱ ደግሞ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳልያ ለመጎናፀፍ በቃ።

ሜክሲኮ በ1968 እኤአ ላይ ባስተናገደችው 19ኛው ኦሎምፒያድ ላይ ሻምበል ማሞ ወልዴ በ10ሺ እና በማራቶን በተጎናፀፉቸው 1 የወርቅና በ1 የብር ሜዳልያዎች ኢትዮጵያ ከዓለም 25ኛ ደረጃ እንድታገኝ አስችሏል። በአበበ ቢቂላ በተከታታይ ሁለት ኦሎምፒክ ድል የተገኘበትን የማራቶን ውድድር ማሞ ወልዴ በድጋሚ አሸንፎ ታሪክ በመሥራት ለሶስተኛ ጊዜ በማራቶን የኢትዮጵያን ክብር አስጠበቀ።

ይህ የማሞ ጀግንነት ለኢትዮጵያውን ኩራትንና ደስታን ሲያጎናፅፉቸው በጋዜጠኛ ሰለሞን የተደረሰውን ‹‹ማራቶን ልእልቷ›› ዜማንም አዘምሯቸዋል። ማሞ አትሌቲክሱን ከአበበ ቢቂላ ቀድሞ ቢጀምርም ስኬታማ ሆኖ በጀግንነት የወጣው እሱን ተምሳሌት አድርጎ ነው።

በሜክሲኮ በተካሄደው 19ኛ ኦሎምፒያድ ላይ ባገኛቸው የብርና የወርቅ ሜዳልያዎች ማሞ ወልዴ ከንጉሳዊው ሥርዓት የሻምበልነት ማዕረግ ተሰጥቶታል። በ1972 እኤአ በጀርመን ሙኒክ ከተማ በተካሄደው 20ኛው ኦሎምፒያድ ለመጨረሻ ጊዜ ኦሎምፒክን በ40 ዓመቱ ለአራተኛ ጊዜ ለመሳተፍ የበቃው ሻምበል ማሞ ወልዴ በማራቶን ሶስተኛ በመውጣት የነሃስ ሜዳሊያ ማግኘት ችሏል።

ሻምበል ማሞ ወልዴ በሩጫ ዘመኑ ቁመቱ 170 ሴንቲሜትሮች ክብደቱ 54 ኪሎ ግራም ነበር። ዋና አሰልጣኙ ከነበሩት ከስዊድናዊው ኢስካነን በኋላ ለረጅም ጊዜያት አብረውት የሰሩት አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባ ናቸው። በ800 ሜትር፤ በ1500 ሜትር፤ በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር የትራክ ውድድሮች ሯጭነት ከ15 ዓመታት በላይ ያሳለፈ ቢሆንም ከፍተኛውን ስኬት ሊያገኝ የበቃው በማራቶን ነበር።

በሩጫ ዘመኑ ከ15 በላይ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ያሸነፈ ሲሆን በኦሎምፒክ ከተሳተፈባቸው የማራቶን ውድድሮች ባሻገር በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ከተሞች በሚደረጉ የጎዳና ላይ ሩጫዎችና ግማሽ ማራቶኖች፤ በቦስተን፤ በአቴንስ ማራቶኖች መሮጡንም ከሕይወት ታሪኩ ለመረዳት ተችሏል። በመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ፈር ቀዳጅ የሆነው ማሞ ወልዴ ኢትዮጵያ በውድድሩ የተሳትፎ ታሪኳ የመጀመሪያውን ሜዳሊያ እንድታገኝ ማስቻሉ የሚጠቀስ ጉልህ ታሪኩ ሲሆን በ5,000 ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ሲወስድ ኢትዮጵያን በአትሌቲክስ የደረጃ ሰንጠረዥ 12ኛ፣ ላይ ባጠቃላይ ስፖርት 18ኛ ላይ ማስቀመጡ ይታወሳል።

ከንጉሳዊው ሥርዓት በኋላ የደርግ መንግሥት ስልጣን ሲይዝ፤ የክቡር ዘበኛ አባል የነበረው ሻምበል ማሞ ወልዴ ከአብዮቱ ርምጃ ሕይወቱን ያተረፈው በኦሎምፒክ ባገኛቸው የሜዳልያ ክብሮች ነበር።

ከደርግ በኋላ ኢህአዲግ የመንግሥት ስልጣንን ሲረከብ የሻምበል ማሞ ወልዴ የሕይወት ውጣውረድ ወደ አሳዛኝ ምዕራፍ ተሸጋገረ። በቀይ ሽብር ወንጀል ተከስሶ ፍርድ ቤት ቀረበ። የክሱ ሂደት ከ9 ዓመታት በላይ የፈጀ ሲሆን በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ሲፈረድበት የ6 ዓመት እስር ተወስኖ በወህኒ ቤት እንዲቆይ ተደረገ። በእስር ቤት ቆይታው ባገኘው አጋጣሚ ከወንጀል ንፁህነቱን በይፋ ሲናገር ቢቆይም የሚጠበቀውን ምህረት ሊያገኝ አልቻለም።

በኢትዮጵያውያን፤ በስፖርት ቤተሰቡና አፍቃሪዎቹ ከኦሎምፒክ ጀግንነቱ በተያያዘም እንዲፈታ ከአየአቅጣጫው ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም ነበር። ነገር ግን ከፍርዱ በላይ ተጨማሪ 3 ዓመታት በእስር በመቆየቱ ወዲያኑ እንዲፈታ ተወስኖ ከ9 ዓመት እስር በኋላ ነፃ መሆን ችሏል።

በመጨረሻም በትራክ፣ በሀገር አቋራጭ እና በጎዳና ላይ ውድድሮች ከአፍሪካ እስከ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን የወከለው ሻምበል ማሞ ወልዴ በህመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ሆኖም የማሞ ወልዴ የስፖርት ውለታ ከመቃብር በላይ ሆኖ ዘላለም የሚወሳ ነው። ሰላም!

# ስፖርት

## የሜዳሊያ ተስፋ የተጣለበት የወንዶች 3 ሺ ሜትር መሰናክል

**ዓስማየሁ ግዛው**

በ2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ተጠባቂው የወንዶች 3 ሺ ሜትር መሰናክል ውድድር ዛሬ ምሽት ይካሄዳል። ኢትዮጵያ በሶስት ጠንካራ የርቀቱ አትሌቶች ትወከላለች። የወርቅ ሜዳሊያውን ለመወሰድም ከሞሮኮና ኬንያዊያን አትሌቶች ጋር የሚያደርጉት ፉክክር በጉጉት የሚጠበቅ ነው።

የማጣሪያ ውድድራቸውን በጥሩ ብቃት በማለፍ ለፍፃሜ የደረሱት አትሌት ለሜቻ ግርማ፣ ሳሙኤል ፍሬው እና ጌትነት ዋለ ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ሜዳሊያ ለማስመዝገብ ትልቅ ተስፋ ተጥሎባቸዋል። በርቀቱ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ለማስመዝገብ በቡድን ሥራ እና በቴክኒክ ከተፎካካሪያቸው የኬንያ እና የሞሮኮ አትሌቶች ጋር ብርቱ ፉክክር ያደርጋሉም ተብሎ ይጠበቃል።

የወርቅ ሜዳሊያውን ለማስመዝገብ እድል ያለውና ተስፋ የተጣለበት አትሌት ለሜቻ ግርማ ዘንድሮም ከሞሮኳዊው አትሌት ሶፊያን ኤል ባካሊ ከባድ ፈተና ይጠብቀዋል። ወጣቱ አትሌት ለሜቻ በርቀቱ በልምድም ይሁን በቴክኒክ መጎልበቱ እንዳለፉት ዓመታት ለሞሮኮው አትሌት በቀላሉ እጅ ይሰጣል ተብሎ እንዳይጠበቅ አድርጓል። ለሜቻ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም በኦሊምፒክና በዓለም ቻምፒዮና በዛሬው የትራክ ላይ ባላንጣው ቢሸነፍም የርቀቱ የዓለም ክብረወሰን በእጁ ይገኛል። ኤል ባካሊ የቶኪዮ ኦሊምፒክ ድልን ለመድገም የሚሮጥ ሲሆን ለሜቻ ለራሱም ሆነ ለሀገሩ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ የመጀመሪያ የመሆን ጉጉት አለው። የ23 ዓመቱ አትሌት በእድሜና በልምድ ከሚበልጠው ሞሮኮዊ አትሌት የሚገጥመውን



**ለሜቻ ግርማ፣ ሳሙኤል ፍሬው እና ጌትነት ዋለ ዛሬ ምሽት ለሜዳሊያ ይፋለማሉ፣**

ፈተና ባዳበረው ልምድ ታግዞ ወርቁን ለኢትዮጵያ ሊያስገኝ እንደሚችልም ወቅታዊ አቋሙና የከዚህ ቀደም ውጤቶቹ ይናገራሉ።

ሶፊያን ኤል ባካሊ በዚህ ዓመት በጉዳት ምክንያት ሁለት ውድድሮች ብቻ ነው ማድረግ የቻለው። እነሱም በግንቦት ወር በተካሄደው የማራካሽ ዳይመንድ ሊግና በስፔን በተካሄደው የዓለም አቀፍ ሀገር አቋራጭ ውድድር ሶስተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀበት ነው። ለሜቻ በበኩሉ ባለፉት ሶስት ዓመታት በውድድሮች ተወጥሮ በ1500፣ 2000፣ 3000 መሰናክልና በ5000 ሜትር ውድድሮችን በማካሄድ እድገቱን አስመልክቷ። ቶኪዮ ላይ ከኤል ባካሊ ጋር አንገት ለአንገት ተናንቆ በመጨረሻም ለጥቂት ተቀድሞ የወርቅ ሜዳሊያውን ቢነጠቅም ብሩን ማሳካቱ አልቀረም።

ለሜቻ በዓለም የቤት ውስጥ ውድድር ለ25 ዓመታት ማንም ያልደፈረውን ክብረወሰን ከአንድ ደቂቃ በላይ በማሻሻል በእጁ አስገብቷል። በዚህ ርቀት ደግሞ ለ19 ዓመት የቆየውን ክብረወሰንም የግሉ ማድረግ የቻለበትን ታሪክ ሰርተል። በቶኪዮ ኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያውን ለመውሰድ 8፡10፡38 የሆነ ሰዓት ፈጅቶበታል። ይህም ወርቁን የወሰደው ኤል ባካሊ ከገባበት ሰዓት 2 ሴኮንድ ከ30 ማይክሮ ሴኮንዶችን ብቻ የዘገየ ሰዓት ነው።

አትሌት ጌትነት ዋለ እና ሳሙኤል ፍሬውም በተጠባቂው ውድድር ጠንካራ ፉክክር ለማድረግ ይሰለፋሉ። ማጣሪያውን በድንቅ ብቃት ካለፈ በኋላ ጉዳት የደረሰበት ሳሙኤል ፍሬው ግን የመወዳደሩ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው። ያም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች በውድድሩ ሜዳሊያ ለማስመዝገብ ከሚያደርጉት ጥረት ባለፈ ኤል ባካሊን የማዳከም የቤት ሥራ ይኖርባቸዋል። በውድድሩ ብዙ ልምድ ያካበተው ጌትነት ዋለ ባለፈው ቶኪዮ ኦሊምፒክ ተሳትፎው 4ኛ ደረጃን ይዞ ነው ያጠናቀቀው። ሌላኛው የ3 ሺ ሜትር ተወዳዳሪ ወጣቱ አትሌት ሳሙኤል ፍሬው የመጀመሪያው ኦሊምፒክ ውድድሩን የሚያደርግ ሲሆን በኮሎምቢያ ካሊ በተካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አስመዝግቧል። ሶስቱ አትሌቶች በቅንጅት ሰርተው ከሞሮኮና ኬንያ አትሌቶች የሚገጥማቸውን ፉክክር አሸንፈው ተናፋቂውን የወርቅ ሜዳሊያ እንደሚያስመዘግቡም ይጠበቃል።

የወንዶች 3 ሺ ሜትር መሰናክል በኦሊምፒክ መካሄድ የጀመረው እአአ በ1920 ሲሆን ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ሜዳሊያ ያገኘችው በ1980ው የሞስኮ ኦሊምፒክ በሻምባል እሸቱ ቱራ አማካኝነት ነው። ለሜቻ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ቶኪዮ ካስመዘገበው የብር ሜዳሊያ ጋር ኢትዮጵያ ሁለት በርቀቱ የኦሊምፒክ ታሪክ በወንዶች ከዓለም 11ኛ ደረጃን ይዛ ትገኛለች።